# የጠላት ደጆችን መውረስ

እንደምን አደራችሁ፡ ሁላችሁም። ዛሬ ጠዋት ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ፡ ወደ ተበርናክሉ በመመለሴ ደስ ብሎኛል። እንዲህ ነው፡ በአብዛኛው፡ ደጋግመን፡ ወደዚህ ለመምጣት እንሞክራለን፡ እ—እና ለጸሎት ከተለያዩ ቦታዎች ለሚመጡ ሰዎች፡ እንጸልያለን።

አሁንም በቅርቡ፡ አሁን፡ ወደ ካሊፎርኒያ እና ወደ ዌሰት ኮሰት ለሰብሰባዎች እንወጣለን። በዚያም የሰማይ አምላክ ምህረቱን እንዲያሳየን እና ታላቅ አገልግሎት እንዲሰጠን፡ ጸሎት እንድታደርጉልን እንማጸናለን።

ትናንት፡ ወይም፡ ትናንት ማታ፡ የገባሁት፡ አርፍጄ ነበር። እና ትላንትና ከ... ማለቴ፡ ትናንትና፡ እና ከትናንት ወዲያ፡ በህይወቴ ታላላቅ-ከሚባሉ ቀናት ውስጥ አንዱ ነበር። ትናንትና፡ በህንጻው ውስጥ፡ የጌታን መውረድ የተመለከቱ፡ ቢያንስ ሁለት፡ ወይም ሶስት ሰዎች እንደነበሩ አውቄአለሁ። እና ዛሬ ጠዋት፡ ጊዜ ስላልነበረኝ ለእናንተ መናገር አልቻልኩም እንጂ፡ የሆነ ታላቅ ድንቅ ነገር ተከሰቷል። ግን ምናልባት በሚቀጥለው እሁድ ጥዋት፡ ከመሄዳችን በፊት፡ በመልእክቱ ጊዜ፡ እ—እንድነግራችሁ፡ ምናልባት ጊዜ ይኖረኛል። ጌታ ከፈቀደ፡ ቢያንስ ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ፡ እሁድ ጠዋት፡ እዚሁ እቀራለሁ። በሳን ሆሴ፡ ካሊፎርኒያ ለሚደረገው፡ የሳን ሆሴ ስብሰባ፡ ከተቻለ እኩለ ቀን አካባቢ ጉዞ መጀመር እንፈልጋለን። እናም በዚያ በምዕራባዊው የባህር ዳርቻ፡ ምናልባት ዘመዶች ካሏችሁ፡ ምናልባት፡ ይህ ለብዙ ጊዜ ሰጠብቀው የኖርኩት፡ በአገልግሎቴ ውስጥ፡ ለውጥ የሚመጣበት ጊዜ እንደሆነ፡ እናምናለን። እናም በጣም ተቃርቧል፡ ትላንትና ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር። እናም አሁን ወዲያውኑ እንደሚሆን አምናለሁ፡ እና እስካሁን ድረስ፡ ካየነው ወይም ከሰማነው ሁሉ በላይ እጅግ የላቀ ይሆናል። ስለዚህ፡ አስታውሱ፡ ይህም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። አያችሁ? እና ስለዚህ እየጠበቅነው ነው፡ በማንኛውም ጊዜ።

ሰብሰባውም በዚያ በመዝናኛው ሜዳ ላይ እናደርገዋለን። ልክ ነው፡ ብዬ አስባለሁ፡ አይደል ጂን? በሳን ሆሴ፡ ካሊፎርኒያ በሚገኘው መዝናኛ ሜዳ ላይ። እና በ—በሳን ሆሴ ውስጥ፡ ከ 20 ጀምሮ፡ እስከ 29 የሚቆይ፡ የአሰር-ቀናት ሰብሰባ ይሆናል። እንግዲህ፡ አስታውሱን ደግሞም ጸልዩልን።

አሁን አገልግሎቱን ለመጀመር፡ በሰዓቱ ከሄድን፡ ለታመሙ ለመጸለይ፡ እና ቃሉን ለማምጣት አንድ ሰዓት ተኩል ያህል አለም። ዛሬ ጠዋት፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ አነስ ያለች ጽሑፍ፡ መርጫለሁ፡ በመጽሐፍ ክዱስ ሁለት ክፍሎች ላይ፡ እናገራለሁ።

ከመናገራችን በፊት ግን፡ ለጸሎት፡ ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

2 ቸር አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት የማይገባን ልጆች ሆነን፡ በጸጋህ ዙፋን ፊት በትህትና እንመጣለን፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ በተሰጠን፡ በእግዚአብሔር ላይ ያልተበረዘ እምነት፡ እና በዘላለማዊ ህልውናው፡ እና በጌታ በኢየሱስ በኩል በገባው ቃል ኪዳን ከእኛ ጋር ነውና፡ በትህትና መጥተን ማንኛውንም

ነገር በሰሙ ብንለምን፡ ልመናችንን ይሰጠናል። qስለዚህ፡ እኛ ስላደረግነው መልካም ነገር ነው ብለን ወደ ኋላችን አንመለከትም፡ እኛ ያደረግነው ነገር የለምና፡ ነገር ግን ጸጋችን በእግዚአብሔር ልጅ በነፃ ወዳገኘንበት፡ የቀራኒዮ ውለታ መለስ ብለን እንመለከታለን። እናም እኛ የማይጠቅሙ ሰዎች ስንሆን ከእርሱ ጋር ህብረት ይኖረን ዘንድ፡ ወደ እግዚአብሔር እጅግ መቅረብ እንድንችል፡ በዚያ በቀራንዮ በጸጋው ለእኛ ያንን ማድረጉ፡ ስናስበው፡ ጉሮሮአችንን አልፎ የሚፈሰውን እንባችንን፡ መቆጣጠር አንችልም። ስለዚህ አሁን እኛ ለእርሱ ወንዶች እና ሴቶች ልጆቹ ነን።

3 እናም ዛሬ ጠዋት፡ ጌታ ሆይ፡ በዚህች ትንሽ ጣሪያ ስር፡ ለአገልግሎት እና፡ እራሳችንን ልንሰጥ መጥተናል፡ ኃጢአታችንን ለመናዘዝ፡ እና—እና ለመለኮታዊ አምልኮ መጣን። ከእኛ ጋር እንደምትሆን እናም ስለ መምጣትህ መንፈሳዊ ግንዛቤ እንደምትሰጠን እናምናለን፡ ይህም ለሺህ አመታት ሲጠበቅ ለነበረው ታላቅ ክስተት በየቀኑ ልባችንን እናዘጋጅ ዘንድ ነው። በእውነት ፍጥረት ሁሉ ደግሞ በመቃተት፡ ስለ ነጻነት ያለቅሳልና። በውስጣችን ያለው መንፈሳችን፡ ጌታ ሆይ፡ ያለማቋረጥ ይናዘዛል፡ እንዲህ በማለት፡ “እኛ እንግዶች እና መጻተኛዕች ነን፡ ይህ መኖሪያችን አይደለም፡ ነገር ግን ገንቢዋ እና ሰሪዋ እግዚአብሔር የሆነችውን ከተማ እንጠብቃለን።” የሚመጣውን ታላቅ ጊዜ እንጠብቃለን።

4 ጌታ ሆይ፡ በእነዚህ ሰብሰባዎች ልመናችን፡ እዚህ ስንሰበሰብ፡ ስለታመሙና ስለተጨነቁ ልጆችህ እንጸልያለን። እና በመካከላችን ያሉትን ሁሉንም በሽታዎች እና ደዌዎች ለመፈወስ፡ ዛሬ ልዩ በሆነ መንገድ ከእኛ ጋር እንድትገኝ እንጠይቅሃለን። ምናልባት፡ ጌታ ሆይ፡ ቀደም ብዬ የተናገርኩትን ይህ የተሰፋ ቃል፡ ትናንትና ጎህ ሲቀድ፡ ከአንተ ጋር በጉባኤው እንደተናገርኩት፡ አንተም አቤቱ በድንቅ መንገድ ደጋግመህ አረጋግጠኸዋል። እና ጊዜው በጣም ቅርብ እንደሆነ ይሰማናል። እናም ይህ ቀን፡ ጌታ ሆይ፡ የሚፈጸምበት ቀን ይሁን፡ አቤቱ አገልግሎትን የምትቀይርበት፡ ጌታ ሆይ፡ ለህዝብህ የበለጠ መሐሪ ወደሆነ ነገር የምትቀይርበት ቀን ይሁን።

5 አሁንም፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ለእነዚህ ብቻ ሳይሆን፡ በአለም ዙርያ ላሉ ሁሉ፡ በሰጋዊም ሆነ በመንፈሳዊም ችግር ለተቸገሩ ሁሉ፡ እንጸልይላቸዋለን። በዚህ ዘመን ልጆችህ እየታገሉ ነውና፡ ጌታ ሆይ፡ የልባቸውን መሻት፡ አቤቱ ሰጣቸው። የጠላት ጫና እጅግ ጠንካራ ነውና፡ አንተ ግን ይልቅ ጠንካራ ነህ። “በዓለም ካለው ይልቅ በአንተ ያለው ታላቅ ነው፡” ተብሎ ተጽፎአልና። በዚህም ድል እንነሣለን። አቤቱ በተጻፈው ቃልህ ተናገረን። ዛሬ ጠዋት ከዚህ ሰንወጣም፡ እነሆ እንደ ኤማሁስ መንገደኞች እንዲህ መናገር ይሁንልን፦ “በመንገድ ሲናገረን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ” የተሰፋውን ቃል በሰጠ፡ በኢየሱስ ሰም እንጠይቃለን። ኣሜን።

6 አሁን ከኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ከሁለት ቦታዎች አነባለሁ። አንደኛው በ 24ኛው ምዕራፍ ይገኛል፡ ከቁጥር 56 ይጀምራል፡ እንዲህ ይነበባል።

**እርሱም፡ እግዚአብሔር መንገዴን አቅንቶልኛልና፡ አታዘግዩኝ፥ ወደ ጌታዬ እሄድ ዘንድ አሰናብቱኝ አላቸው።**

**እነርሱም፡ ብላቴናይቱን እንጥራና፡ ከአፍዋ እንጠይቅ አሉ።**

**ርብቃንም ጠርተው፡ ከዚህ ሰው ጋር ትሄጂለሽን፡ አሉአት? እርሰዋም፡ እሄዳለሁ አለች።**

**እኅታቸውንም ርብቃን** ከ-... ከእህታቸው ጋር፡ **ሞግዚትዋንም፡ የአብርሃምን ሎሌና ሰዎቹንም አሰናበቱአቸው፡...**

**ርብቃንም መረቁአትና፡ አንቺ እኅታችን፡ የእልፍ ሚሊዮን እናት ሁኚ፡ አሏት፡ ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረስ አሉአት።**

7 በዘፍጥረት 22 ላይ፡ 15ኛው ቁጥር ደግሞ፡ እናነባለን።

**የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፥**

**እንዲህም አለው፡ እግዚአብሔር፡ በራሴ ማልሁ ይላል፡ ይህን ነገር አድርገ**ሃልና፡ **አንድያ ልጅ**ህንም፡ **ልጅህንም አል-...** አል**ከለከልህምና፥**

**በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፡ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት... አበዛዋለሁ፡ በባሕር ዳር እንዳለ... አሸዋም አበዛዋለሁ፥ ዘርህም** የጠላቶችን **ደጅ ይወርሳል፥**

**የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተ**ሃልና**።**

8 አሁን ጌታ በተነበበው ቃሉ ላይ በረከቱን ይጨምር። አሁን ርዕስ ከተፈለገ፡ ይህን መውሰድ እፈልጋለሁ፡ የዛሬ ጠዋት ርዕስ ጉዳይ፡ በመጀመሪያ፡ "ቃል በተገቡት ደጆች ፊት መፈተን፡" ነው። ርዕሱም፥ **የጠላት ደጆችን መውረስ** ይሆናል።

9 እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሰጥቶት ስለነበረ፡ ይህን አባት ፈተነው። እግዚአብሔር ቃል ሲገባ፡ የተናገረውን ወይም የገባውን ቃል ከመፈጸሙ በፊት፡ ይህ ሰው ለተሰፋው ቃል የሚገባ መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋል። ስለዚህ አብርሃም በዘሩ በኩል አለም ሁሉ እንደሚባረክ፡ ወንድ ልጅም እንደሚወልድ ቃል ተገብቶለት ነበር። እናም፡ ይህ ልጅ፡ ከእርሱ ዘንድ ምድርን ሁሉ የሚባርክ ዘር ይወጣል። አብርሃምም፡ ተስፋ በተሰጠው ጊዜ፡ የሰባ-አምስት ዓመት ሰው ነበረ፥ ሚስቱ፡ ሣራም፡ የስድሳ-አምስት ዓመት ሴት ነበረች። መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ አብርሃም ባለማመን በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል እንዳልተደናቀፈ ይነግረናል፡ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ግን፡ በረታ። እግዚአብሔርም፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ፡ ፈተነው፡ እርሱ ግን በረከቱ ከመፈጸሙ በፊት ወደ ነበረች ወደ መጨረሻዋ ፈተና ደረሰ።

10 የአብርሃም ዘር በሆኑት ሁሉም ጋር እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር የተሰፋውን ቃል ከመሰጠቱ በፊት ያንን የመጨረሻ ፈተና ይፈትነናል። እና የሚቻል ከሆነ፡ እዚህ አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡ በግሌ፡ ያንን እከለክላለሁ። ያ በእሱ ላይ ምን ምላሽ እንደምትሰጡ የማየት፡ የመጨረሻ ፈተና። ይህንንም ፈተና ለአብርሃም በሰጠው ጊዜ፡ አብርሃምን ሲጀምር እንደነበረው ታማኝ ሆኖ አገኘው። የፈውስን ቃልኪዳን የምንቀበል ከሆነ ዛሬ

ጠዋት ምንኛ መታደል ነው እዚህ ቆመን እንደተቀበልነው ልክ በታማኝነት ይጸናልና። ዶክተሩ ምንም ይበል፡ ታምናችሁ ቁሙ።

11 ይህንንም ባደረገ ጊዜ፡ አንድያ ልጁን አልከለከለም፡ ነገር ግን ምስክሩን ለመግደል፡ ቢላዋውን በይስሐቅ ደረት ውስጥ ሊሰካው ነበር። በሚያውቀው ምድር ሁሉ፡ ይህን ልጅ እንደሚወልድ፡ መሰክሮ ነበርና። ከዚያም ልጁ ከመጣ በኋላ፡ በእጥፍ እንዲመልስ ተጠየቀ፡ በዚያም ምስክርነቱ ይፈጸም ዘንድ የነበረውን ብቸኛ ተስፋ ግደል ተባለ። እግዚአብሔርም በእግዚአብሔር ላይ ለነበረው እምነት ታማኝ መሆኑን ባየ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ከሰማያት አየና እንዲህ አለው፡ “እንድባርክህና እንዳበዛህ በራሴ ምያለሁ፡ ዘርህም የጠላቱን ደጅ ይወርሳል።” እንዴት ያለ ቃል ኪዳን ነው!

12 እናም የዚህ አሰደናቂ፡ ይጠበቅ የነበረው፡ እና ቃል የተገባለት ልጅ፡ እናት የሆነችው ርብቃም፡ ከዚህ በፊት አይታው የማታውቀውን ሰው በተመለከተ፡ ለመጨረሻው ፈተና በተጠራች ጊዜ፡ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ብቻ አይታ ነበርና። እና ወላጆቿም ከዚህ ቀደም አይታው ለማታውቅ ሰው ሚስት ለመሆን ከዚህ እንግዳ ጋር መሄድ እንዳለባት፡ ወይም እንደሌለባት ሙሉ በሙሉ መወሰን ሲሳናቸው፡ ወደ መጨረሻው ፈተና ቀረበች። “ብላቴናይቱን ጠርተን እንጠይቃታለን። እሺም ወይስ እምቢ፡ ከአንደበትዋ እንሰማለን።”

13 ወደ እግዚአብሔር ዘር ሁሉ የሚቀርበው በዚህ መንገድ ነው። ከአንደበትህ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ካንተ መሰማት ይፈልጋል።

14 እናም በፈተና ስትፈተን፡ ለአንድ ደቂቃ እንኳን አላቅማማችም። “እሄዳለሁ፡” አለች። ደሰ ሲል። “እስኪ ውስጤን ላዳምጥ። እስኪ ላሰብበት፡” አላለችም። ሙሉ በሙሉ አመነች። እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚፈጽም፡ ሙሉ በሙሉ ስታምኑ እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው ሰዎች እንደነዚህ ያሉ ናቸው። “እሄዳለሁ፡” አለች።

15 እና ህዝቦቿ ያኔ፡ ምናልባት ያላወቁት እንደሆነ እንጂ፡ በታላቅ ቅባት ስር ሆነው፡ እኅታቸውና፡ ልጃቸው በሆነች፥ ቆንጆይቱ አይሁዳዊቷ ወጣት ሴት ላይ፡ እጃቸውን ጭነው እንግዳ ወደ ሆነው ምድር፡ እንግዳ ወደ ሆነው ህዝብ፡ በግመል ላይ ጭነው በላኳት ጊዜ ትንቢት ተናገሩ። ነገር ግን በእነሱ ላይ የሆነ ነገር ነበር። እንዲህም አሉ፡ “ዘርሽ የጠላታቸውን ደጅ ይውረሱ። የእልፍ የእእላፋት እናት ሁኚ።”

16 እናም፡ ዛሬ፡ ያ ህዝብ እና የእግዚአብሔር ህዝብ ዘር ከባህር ዳርቻ እስከ ባህር ዳርቻ፡ በአለም ዙሪያ ተዘርግቷል። በትንሣኤ ጊዜ ሰፍራቸውን ለመያዝ እንደሚወጡ ከዋክብት፡ በሰማያት እንደሚያልፉ፡ እንደ ሰማይ ከዋክብት ይሆናሉ። ሲመጡም፡ በባሕሩ ዳርቻ እንዳለ ይሆናሉ... በባሕር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ ይሆናሉ። በእልፍ የሚቆጠሩ እእላፋት ይኖራሉ።

17 “ዘርህ የጠላቱን ደጅ ይወርሳል።” ይህ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው፡ “የአብርሃም ዘር።”

ስለዚህ፡ በመንፈስ ቅዱሱ፡ እናቱ የልጁ አካል መሆን እንዳለባት አይቶ፡ እንዲሁም፡ የሥጋው አካል ናቸውና። ከዚያም፡ መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ሰዎች በኩል እየሠራ፡ እንዲህ አለ፡ “ዘ... ዘርህ የጠላት ደጅ ይውረስ።”

እንግዲያውስ፡ እግዚአብሔር የጠላትን ደጅ እንደሚወርስ ከማለ፡ ታዲያ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በምን ቦታ ያስቀምጣታል?

18 እኛ የአብርሃም ዘር ነን። ምክንያቱም፡ እኛም፡ በክርስቶስ በሞሞታችን፡ በዚያው በመሐላው ቃል ኪዳን ስር ሆነን፡ የአብርሃምን ዘር ወሰደናል፡ ከእርሱም ጋር ወራሾች ነን። እኛ የአብርሃም ዘር ነን፡ የተሰጠውንም የተሰፋ ቃል ሁሉ ወራሾች ነን። ነገር ግን ፈተናዎቹ ሲመጡ፡ የምንወድቅበት ያኔ ነው። እውነተኛው የአብርሃም ዘር ግን ይወድቃል ብዬ አላምንም። ልክ እንደ አብርሃም ቆራጥ እና ታማኝ ሆነው ይቆማሉ።

19 አሁን እግዚአብሔር ዝም እንደሚል አይተናል ማ—ማለቴ የሚፈጽመውን ካልሆነ በስተቀር ምንም አይነት ቃል ኪዳን አይገባም። እርሱ አምላክ ይባል ዘንድ ያ መፈጸም አለበትና። ከዓመታት በኋላ፡ እኚሁ ሕዝብ፡ የተሰፋው ሕዝብ፡ የአብርሃም ዘር በጉዞአቸው ላይ ሳሉ፡ ወደ ተ—ተሰፋይቱ ምድር እየተጓዙ በነበሩ ጊዜ፡ ከፊታቸው የተጋረጠባቸው፡ የተቋቋማቸው ደጅ ነበረ፡ ያም የገዛ ወንድሙ፡ ሞዓብ ነው፡ እንዲህ አለው፡ "በምድሬ አታልፍም። በምድሬ እንዳታልፍ እጠብቃለሁ።"

20 እነርሱም "ከብቶቻችን ሳርህን ቢበሉ ውኃህንም ቢጠጡ፡ እነሆ እንከፍላለን፡" አሉ።

እርሱ ግን "ይህን ምድር አትሻገሩም፡" አላቸው።

21 የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ግን እውነት እንደሆነ ጸና። እነርሱም ሄደው ነቢያቸውን፡ በለዓምን ይዘው፡ ሕዝቡን እንዲረግም አወረዱት። በዚያም የተናገረው ይህ ነው። የተባረከውን ዘር እጅግ የከፋውን ጎኑን ሊያሳዩት ሞከሩ፡ እግዚአብሔር ግን ከሁሉ የተሻለውን አሳየው። እንዲህም አለ፡ "እስራኤልን የሚረግም ሁሉ የተረገመ ይሆናል፡ የሚባርከውም ሁሉ የተባረከ ይሆናል።" እናም ወጥመዶች ሁሉ ተሰባብረው እነሆ እስራኤል በሜዳዎቹ ተሻገረ። እግዚአብሔር የጠላቱን ደጅ እንደሚወርስ ቃል ገብቷልና።

22 በኋላም፡ በዘመናት፡ በዚህ የንጉሣዊ የዘር ሐረግ ላይ፡ ዘር የነበረው ዳንኤል የሚባል አንድ ሰው መጣ፡ እርሱም የአብርሃም ዘር ነውና፡ በተሰፋው ቃል ዘር ሐረግ ላይ ነበር። እግዚአብሔርም ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ፡ ነቢይ ይሆንለት ዘንድ መርጦታልና፡ ደፋር ሆነ ታማኝም ሆነ። በባዕድ አገርም ቢሆን፡ በልቡ "በእነዚያ ራሴን አላረክሰም፡" ብሎ አሰበ። እውነተኛው የአብርሃም ዘር ማለት ይህ ነው፥ እንግዳ በሆነች ምድር እየኖረ፡ እንግዳ በሆነ ሕዝብ መካከል እየኖረ፡ ለዚያ ለቃል ኪዳኑ ግን ደፋር ሆነ። "በእነዚያ ራሴን አላረክሰም። ታማኝ እሆናለሁ።"

23 እግዚአብሔር እንደ አባቱ እንደ አብርሃም፡ ፈተነው። ንጉሡም እንዲህ አለው፡ "ወይ ከእኛ እንደ አንዱ ትሆናለህ በምንሰግድበት መንገድ ታመልካለህ፡ ወይም የተራቡ አንበሶች ወደ ሞላበት ጉድጓድ እጥልሃለሁ።"

24 ዳንኤልም፡ እንደ አባቱ አብርሃም፡ እንዲህ አለ፡ "ወደ አንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ልትጥለኝ ትችላለህ፡ ግን ለአንዳቸውም ምስሎችህ አልሰግድም። ተራ የሆነውን ሃይማኖትህን አልቀበልም። ለጆሆቫ ታማኝ እሆናለሁ።"

25 እና ያኔ ትዕይንቱ መጣ። ንጉሱም የገባውን ቃል ጠበቀ፡ ነቢዩንም ያዘና ወይም ወሰዶ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣለው። የዳንኤል ጠላቶች፡ አንበሶቹ፡ ወደ ነቢዩ በተጣደፉ ጊዜም፡ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ጠበቀ። የጠላቱን ደጅ ወረሰ። እግዚአብሔርም መልአኩን በዚያ በእነዚያ አንበሶች ፊት አቆመ፡ ደጁንም ወረሰ። እግዚአብሔር ቃሉን ጠበቀ። “የጠላቱን ደጅ ይወርሳል።” እግዚአብሔር ተናግሯልና።

26 በዚያም ለዓላማው ታማኝነታቸውን የሰጡ ሌሎች ሦስት ተጨማሪ ሰዎች ነበሩ፡ በእውነት የአብርሃም ዘር ነበሩ፡ እነርሱም ሲድራቅ ሚሳቅ አብደናጎም ነበሩ፡ ተፈተኑም። እንዲህም አሏቸው፡ “የበገና-ድምጽ እና የቀንደ መለከቱም-ድምጽ ሲነፋ በሰማችሁ ጊዜ ካልሰገዳችሁ፡ ለሐይማኖታችን ባትሰግዱ፡ የቆማችሁለትን የራሳችሁ ጉዳይ—ካልካዳችሁ! በመስረቱም፡ ተዳክማችኋል። ከእንግዲህ ሐይማኖታችሁ ከማንም አይለይም።” ይህን ሁሉ ጊዜ አንሰማው? የ—የኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ግን ልዩ ነው። የትንሣኤው ኃይል ልዩ ነው። እኛ የተለየ ሕዝብ፡ ልዩ ሕዝብ፡ የንጉሥ ካህናት ነን። እግዚአብሔር ልዩነቱን ያደርጋል።

27 ነገር ግን “ከእኛ ጋር አንድ መሆን አለባችሁ፡” ሲሏቸው። ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ከእነርሱ አንዱ መሆን ቢፈልጉ መሆን ይችሉ ነበር፡ ይሁን እንጂ ከእርኩሶቹ ዘንድ መሆን አልፈለጉም። አሁን፡ እንዲህ አሏቸው፡ “እንግዲህ ካልሰገዳችሁ፡ ወደ እቶን የሚያሰገባ ደጅ አዘጋጅተናል፡ እኛም እንከፍተዋለን ወደዚያም እንጥላችኋለን፡ ያን ጊዜ እናንተም ከእነርሱ ወገን በሆንን ብላችሁ ትመኛላችሁ።”

28 እነርሱም የገባውን ቃል ኪዳኑን አሰቡ። ወደ እቶንም አወረዱአቸው። በሩን ከፍተው ወደ እሳቱ በጣሉአቸው ጊዜ፡ ያም ጠላታቸው በላ፡ የጠላታቸውን ደጆች ወረሱ። እግዚአብሔር ልጁን ወደ እነዚያ የእሳት ነበልባል ልኮ ነፋሱን አቀዘቀዘው፡ በዚያም ሳሉ ተናገራቸው። የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ጸና። የጠላትን ደጅ ወረሱ። በመጀመሪያ ተፈተኑ፡ ከዚያ የጠላትን ደጅ ወረሱ።

እንዲህ በማለት ቃል የገባው ኢየሱስ አይደለምን? “ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንኳ ከምትበድል፡ የወፍጮ ድንጋይ በአንገትህ ላይ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ብትወረወር ይሻልሃል። በእኔ በሚያምኑት በእነዚህ ታናናሾች በደልን አታምጣ። በእኔም የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።”

29 ልዩነት ፈጥሯል። ያመነውን ያላመነውን አሳይቷል።

እና፡ ሁል ጊዜ፡ ሦስት አይነት ሰዎች አሉ፡ እነዚያም፡ እምነት የሌላቸው፣ አስመሣይ-አማኞች፣ እና አማኞች ናቸው። እግዚአብሔር ግን አማኝ ማን እንደሆነ የሚያረጋግጥበት መንገድ አለው። ያ አማኙም እግዚአብሔር እውነት ነው በሚለው ላይ ጸንቶ ይቆማል። አዎን።

30 ቴሰብያዊው፡ ኤልያስ ነበር፡ ወደ ትዕይንቱ በመጣ ጊዜ፡ ለእግዚአብሔር የሚኖር እርሱ ብቻ እንደሆነ እስኪያስብ ድረስ ደርሶ ነበር። ንጉሱም ለፍርድ ሊያቀርበው ፈልጎ ነበር። እናም አሳደዱት። ያቺ ክፉ፡ ኤልዛቤል የተባለች፡ የተቀባባች-ንግስት፡ ህይወቱን አደጋ ላይ ጣለች። ወደ ትዕይንቱ በመጣ ጊዜ፡ ኤልያስ የጠላቱን ደጆች ወረሰና ሕዝቡን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መለሰ። እግዚአብሔር የገባውን ቃል ይጠብቃል።

31 ሙሴ ደግሞ፡ በዚህ በንጉሣዊው የዘር ሐረግ ውስጥ ዘር በሆነ ጊዜ፡ የአብርሃም ዘር ከሆነ በኋላ፡ የእስራኤልን ልጆች ያድን ዘንድ፡ ወደ ግብፅ በወረደ ጊዜ፥ እግዚአብሔርም ምድርን ይመታ ዘንድ፡ ምልክትና ድንቅ ሰጠው፡ እና እንቁራሪቶችን፡ እና ቁንጫዎችን፡ ጨለማን፡ በረዶን፡ ዝናብን፡ እና እሳትን አወረደ፡ እናም እነዚህን ሁሉ ተአምራት አድርጓል። ሆኖም፡ በጆሆቫ እጅ ባወጣቸው ጊዜ፡ በእርሱና በተሰፋይቱ ምድር መካከል ያለውን ደጃፍ የተጋፈጠበት ጊዜ መጣ። በመንገዱ ማዶ፡ የቀይ ባህር ደጅ ነበረ። በፈርዖን ጦር፡ በተራሮች፡ እና በበረሃዎች እና በቀይ ባህር፡ ተከበቡ። ሙሴ ግን ወደ ፊት ወጥቶ የጠላቱን ደጅ ወረሰ፡ በደረቅ ጫማ፡ ምድርን እየረገጠ፡ ቀይ ባህርን ተሻገረ። "የጠላትን ደጅ ይወርሳል።" እግዚአብሔር ተናግሯልና፡ አራት ነጥብ።

32 ብዙም ሳይቆይ ከጥቂት አመታት በኋላ ፈተናዎቹ መጡ፡ ለሰዎች ጉባኤ ቀላል ሆኖ ሳለ፡ ነገሮች መሆን ባለባቸው መንገድ ሳይሆኑ በቀሩ ጊዜ ቤተክርስቲያኒቱ ተናወጠች። እግዚአብሔር እንደዚያ እንዲሆን ፈቅዶታልና። እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ ነውጥን ያመጣል፡ "ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ ልጅ ሁሉ መፈተን አለበትና፡ መፈተሽ፡ እና መታየት አለበት።" በሽታ እንዲመታህ ይፈቅዳል። በእውነት የአብርሃም ዘር መሆናችሁን፡ ለአለም ለማሳየት ደዌዎች እንዲመጡባችሁ፡ እንዲፈትናችሁ እና እንዲፈትሻችሁ ይፈቅዳል። በራሱ ፈቃድ እንዲሆን ይፈቅዳል። አደጋዎችን ይፈቅዳል። ወዳጆች እንዲቃወሙህ ይፈቅዳል። እነዚህን ሁሉ ይፈቅዳል፡ ይፈትናችሁ ዘንድ፡ ዲያብሎስን ይለቅባችኋል። ከህይወታችሁ በቀር ሌላው ሁሉ ያደርግባችኋል። በመከራ አልጋ ላይ ሊጥላችሁ ይችላል። ጎረቤቶቻችሁን በእናንተ ላይ ሊያነሣሣ ይችላል። ቤተ ክርስቲያንን በእናንተ ላይ ሊያነሣሣ ይችላል። ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል፡ እና እሱን እንዲያደርግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ይህም ለእኛ፡ ከወርቅ ይልቅ የሚበልጥ እንደሆነ ተምረናል።

33 አብርሃም ከይስሐቅ ጋር፡ በተራራው ላይ፡ ለእርሱ ተሰጥቶት የነበረው ተስፋውስ? እና በታማኝነቱ እና በእውቀቱ፡ በጆሆቫ ላይ በነበረው እምነት ጭምር፡ በዚያ፡ እና በዚያ ብቻ፡ እግዚአብሔርም አየውና "ዘሩ ደጆችን ይወርሳል። እነዚህን ነገሮች እንደማደርግ በራሴ ማልሁ፡" አለ። ይምልበት ዘንድ ከእርሱ የሚበልጥ ሌላ አልነበረምና፡ በራሱ ማለ።

እንግዲያውስ፡ አብርሃም እስከ መጨረሻው ነጥብ ድረስ እንዲፈተን ከፈቀደ፡ እኔን እና እናንተን እስከ መጨረሻዋ ነጥብ ድረስ፡ ሁሉም ነገር እስኪወስድባችሁ ነጥብ ድረስ ይፈትነናል። ብቻችሁን ያስቀራችኋል። ሃሌ ሉያ! አራት ነጥብ።

34 ብቻችሁን ትሆናላችሁ። ወጥታችሁም እንዲህ ትላላችሁ፡ "ቢገድለኝም እንኳ፡ አምነዋለሁ።" የአብርሃም ዘር ያ ነው። ቃል ኪዳኑን የሰጠው እርሱ ነው። "ሌሎች ምንም ቢሉ፡ ሌሎች ምንም ቢያደርጉ፥ እኔ እና ቤቴ ግን፡ እግዚአብሔርን እናመልካለን።" ሌሎቹ፡ "ሁሉም እንዲህ ቢሉ፡ 'ልምምዱ ተራ ነገር ነው። ፈንጠዚያ ብቻ ነው' ቢሉ፥ እኔና ቤቴ ግን፡ እግዚአብሄርን እናመልካለን።"

እና እዚህ ጋር ከጳውሎስ ጋር ልነሳና፡ እንዲህ ልበል፡ "እኔም 'መናፍቅነት' ብለው በሚጠሩት መንገድ የአባቶቻችን አምላክን አመልከዋለሁ።"

“በቤተክርስቲያን ወሬኞች ቢገቡም፡ ጠማማዎች ቢበዙም፡ በሕዝቡ መካከልም ወደ ቤተክርስቲያን ሁሉም ዓይነት ሐሰተኛ ነቢያት ቢገቡም፡ እንዲሁም ጎሮቤቶች በሙሉ እንዲሁ ቢሆኑም እንኳ፥ እኔ እና ቤቴ ግን፡ ጌታን እናገለግላለን። ሁሉም መምጣታቸውን ቢያቆሙም፡ ቤተ ክርስቲያኒቱም ብትቀዘቅዝ፡ ደንታ ቢስ ብትሆን፡ እኔ እና ቤቴ ግን፡ ጌታን እናገለግላለን። አንድ ሰው ተጸልዮለት ባይሻለው እንኳ፥ ክከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውምና፥ እኔ እና ቤቴ ግን፡ ጌታን እናገለግላለን።” ፈተናዎች እና መከራዎች።

35 ሰዎች የማይሳሳቱ አይደሉም፡ እግዚአብሔር ግን አይሳሳትም። ሰው ሆይ፡ አሳብህን በሰው ላይ ከጣልክ፡ ስሕተትን ያደርጋል። ምናልባት ሆን ብሎ ላይሆን ይችላል፡ ቢሆንም ይስታል። እምነትህን ከሰው እንዲያርቅ እግዚአብሔር ይህ ይሆን ዘንድ ፈቀደ። እምነታችን በሰው ጥበብ ላይ ሳይሆን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ኃይል ላይ ነው። እውነተኛዕቹ የአብርሃም ዘር ተሰፋ ቃላቸውን የሚጥሉት በዚያ ነውና። ምክንያቱም፡ የአብርሃም ዘር ሊሆኑ የሚችሉት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ብቻ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ የአብርሃም ዘር አይደሉም። ያ በአብርሃም ዘንድ የነበረው እምነት ወደ አማኙ ይመጣልና። ምንም ቢፈጠር ወይም ተቃራኒ ቢሆን፡ አማኙ በቀጥታ ይዘልቃል።

36 ሰላዮቹም ወደ ኋላ ተመልሰው፡ “ኦህ ይ—ይህ መሞከር ሞኝነት ነው። ከዚህ በላይ መቀጠል አያስፈልግም፡ ምክንያቱም እዚያ ያሉ ሰዎቹ ግዙፍ ሰዎች ናቸው። እናም ታላላቅ መንግስታትን አሏቸው፡ እና ጦ—ጦር አላቸው፡ እኛ፡ ከጎናቸው ስንቆም፡ እንደ አንበጣ እንመስላለን።”

37 እንጂ ብቻ፡ ቢሆንም ስለ ኢያሱ ሳስብ እንዲሁ እንደ ሚጢጢ ድመት አነሰ ያለ እንደሆነ እምናለሁ፡ እንዲሁ አጭር፡ አነስ ያለ ሰው ይመስለኛል። በሆነ ሳጥን ነገር ላ—ላይ፡ ሲወጣ ይታየኛል፡ ወጥቶም ሁለት ሚልዮን ለሚያክል ህዝብ፡ “ሰዎች እና ወንድሞች ሆይ፡” “እኛ ወጥተን መውረስ እንችላለን፡” አላቸው። አያችሁ? ለምን? የአብርሃም ዘር ስለ ነበረ። እግዚአብሔር ቃል ሰጥቷል። ያም ርስታቸው ነበር። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ሰጥቷልና። ተቃውሞው ምንም ቢሆን፡ እውነተኛው የአብርሃም ዘር፡ “እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ልንወርስ እንችላለን” ይላል።

38 እነሆ ዛሬ ጠዋት ቆማችኋል። የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ቆማለች። ማንም ምንም ቢል ግድ የለኝም፡ ሐኪሙ ምንም ቢል፡ ወይም ሌላ ሰው ቢናገር፡ እምነት አልባው ምንም ቢናገር፡ የሚመጣውን ማንኛውንም ነገር ለመጋፈጥ ከአሸናፊዎች በላይ ነን። እኛ የአብርሃም ዘር ነን፡ ጠላት ምንም ቢሆን፡ የጠላታችንን ደጅ እንወርሳለን። እግዚአብሔር ተሰፋ ቃሉን ሰጥቷል። ርስታቸውም፡ ያ ነው።

39 ፈውስ ርስታችሁ ነው። መዳን ርስታችሁ ነው። መንፈስ ቅዱስ ርስታችሁ ነው። እና ዛሬ በምድር ላይ፡ “እንዲህ አይደለም፡” የሚሉ፡ ታላላቅ ሰዎች እና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰባኪዎች እና ሌሎችም አሉ። የአብርሃም ዘር ግን እንደዚያ እንደሆነ ያውቃል። ገብተው የጠላትን ደጆች ይዘዋል። እንደሚወርሱት እግዚአብሔር ተናግሯልና። ቃል ኪዳን ስለሆነ ያምናሉ። “ዘሩ የጠላትን ደጅ ይወርሳል።” አሁን በፈተናዎች፡ እና በመከራዎች ታልፋላችሁ።

40 ኢያሱም፡ ታምኖ በዚያ ጸና። ይህ ትንሽ ሰው “ምንም ቢገዝፉ አይገደኝም፡” አለ። ምንም አይነት ጦር ቢታጠቁ አይገደኝም፡ የከተሞቻቸው ቅጥር ቢረዝምም፡ ታላቅ ቢሆንም አይገደኝም፣ ለእኛ የተሰጠን የተሰፋ ቃል፡ እንዲህ ነውና፡ ‘ደጁ በእግዚአብሄር ዘር ልጆች ይወረሳል፡’ እኛም ሄደን እናሸንፋቸዋለን። ከእነርሱ ጋር ለመፋለም ከበቂ በላይ የመገዳደር አቅም አለን።” ኦህ፡ እውነተኛው ዘር ማለት ይህ ነው።

41 በተፈጥሮ ከተወለዱት ዘር፡ ብዙዎቹ፡ “እኛ አንችልም። መሞከር አያስፈልገንም። አያችሁ፡ በቁጥር አነስተኞች ነን። ከደረጃ በታች ነን፥ እንዲህ እና እንዲያ ነን፡” አሉ። ምንም፡ እንዲህ ቢላቸው እንኳ... አይታቸው ሁሉ... አይኖቻቸው በሚያየው አደረጉ። ኢያሱ ግን እግዚአብሄር በተናገረው ነገር ላይ አየ።

42 የአብርሃም ዘር የትኛውንም የተፈጥሮ ነገር አይመለከትም። ጌታ የተናገረውን ይመለከታሉ። ይህም ተሰፋ ቃሉ ነው። አብርሃም ወደ ተፈጥሮው ቢመለከትስ? የአንድ መቶ ዓመት ሴት... ዘጠና፡ ነበረች። እርሱም መቶ ነበር። ከልጅነቷ ጀምሮ ከእርሰዋ ጋር ይኖር ነበር፡ እርሱም እርሱም ወጣት ልጅ ነበረ፡ ዘር አልነበረም። እነዚያን ነገሮች አልተመለከተም። እርሱ የሚመለከተው እግዚአብሔር ያለውን ብቻ ነውና፡ እነዚያን ነገሮች እንደሌሉ ቆጥሯቸው ነበር። “አብርሃም ሆይ፡ እባርክሃለሁ፡ እነሆም ከሣራ ዘር እሰጥሃለሁ።” እርሱም አመነ። ወደ ተቃዋሚዎች አትመልከቱ። እግዚአብሔር የተናገረውን እንመለከታለን። እግዚአብሔር ተናግሯል፡ አራት ነጥብ።

43 ኢያሱም የሠራዊቱ-ዋና-አዛዥ በሆነ ጊዜ፡ ወደ ዮርዳኖስ በወረደ ጊዜ፡ ወደ ውኃው ዳርም ወርደው ማደውን አማትረው ኢያሪኮን አዩአት። በመካከላቸው ግን፡ ኢያሱ ሠራዊቱን ባዘጋጀ ጊዜ፡ ደጅ ገጠማቸው። ያ ደጅ ዮርዳኖስ ይባል ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ግን በደጆች ሁሉ መልካም ነው። የቱንም ያህል ደጅ ቢገጥማችሁ፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መልካም ነው። “የጠላቱን ደጆች ይወርሳል።” አራት ነጥብ።

በዚያም ጠዋት ወደ ዮርዳኖስ በወረደ ጊዜ፡ ምናልባት፡ ዲያቢሎስ የደመና ማዕበል በየቦታው አንጣልሎ እንደነበረ እምናለሁ፡ ዘመናት ያስቆጠሩ የሚንከባለሉ የጭቃ-ደለሎች ሞልተው፡ ማሳዎቹ ሁሉ በጎርፍ ተጥለቅልቀዋል። ኦህ፡ ከባድ የፈተና ጊዜ ነበር! ኢያሱ ግን ‘የእግዚአብሔርን ክብር ታያላችሁና፡ ተዘጋጁ፡” አላቸው። እናም ሁሉም ነገር ተቃራኒ በሚመስልበት ጊዜ፡ ራሳቸውን ቀድሰው ተዘጋጁ። እግዚአብሄር “ደጁን አሳልፌ እሰጠዋለሁ፡” በማለት የማለለት፡ የአብራሃም ዘር ነው። እርሱም ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡ ያም የእርሱ ደጅ ነበረ፡ ወረሰውም።

44 እነሆ እኔም ከእነዚህ ማለዳዎች አንዱ ላይ ወደ መጨረሻው ደጅ እመጣለሁ። ወደ ዮርዳኖስ ትመጣላችሁ፡ የአብራሃም ዘር የሆነው ብቻ ደጁን ይወርሳል። ምንም ቢሆንም፡ የጠላት ሁሉ ደጅ ይወርሳል።

45 እነዚህ ሁሉ ሰዎች ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። ሰፍራቸው ላይ ሞቱ። ነገር ግን፡ በመጨረሻ፡ በይሁዳ ቤተልሔም አንድ ቀን፡ የንጉሣዊው ዘር ተወለደ። ሌሎቹ ሁሉም፡ የእርሱ ጥላዎች ብቻ ነበሩ። የንጉሣዊው ዘር የተወለደው፡

ከሰው አይደለም። እርሱ ግን ሞትን እና ሲኦልን ድል ለማድረግ፡ ኃይል በደም ስሮቹ ውስጥ ሆኖ፡ በድንግልና ተወለደ። እግዚአብሔር ቃል ገባ። ተራ ሰው ይህን ማድረግ አይችልምና። እግዚአብሔር ቃል ከገባ ግን፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ከአብርሃም ጋር የነበረው ያው አምላክ ነው፡ ያሕዌ-ይርኤ፡ ደጁን የሚወርሰበትን መንገድ ያዘጋጃል። እኛ ይህ እንዴት እናደርገዋለን? ኢያሱ ሞተ። ሙሴ ሞተ። ሌሎቹ ሁሉ ሞቱ። እግዚአብሔር ግን፡ "የጠላቱን ደጅ ይወርሳል" አለ። ሞትንስ እንዴት ያሸንፋል? ነገሮችን የሚሰራበት መንገድ አለው። "የጠላቱን ደጅ ይወርሳል።"

46 የንጉሣዊው ዘር ተወለደ። እንደ እኛ በሁሉም መንገድ ተፈትኗል። መፈተን እንደነበረባችሁ፡ እርሱም እንዲሁ ሆነ። መንፈስ ቅዱስን በተቀበለ ጊዜ፡ ዲያብሎስ ፈጥኖ፡ ለመፈተን፡ አርባ ቀንና ሌሊት ወደ ምድረ በዳ ወሰደው። ከዚያም በወጣ ጊዜ... እናም በሞቱ ወቅት፡ በእጆቹ ላይ ምስማሮች ቸነከሩበት፡ ፊቱ ላይ ተፋበት። በየበሽታዎች ሁሉ አለፈ። ነገር ግን እዚህ ምድር ላይ ሳለ፡ በሽታን ማሸነፍ እንደሚችል አረጋገጧል። የጴጥሮስ አማች፡ በትኩሳት ሽባ በሆነች ጊዜ፡ እጇን ዳሰሰ እና ንዳዱ ለቀቃት። ለምጻሙ በር ላይ "አንጻኝ! አንጻኝ! ብትወድስ፡ ልታነጻኝ ትችላለህ፡" አለ።

47 እርሱም፡ "እወዳለሁ፡ ንጻ" አለው። እነሆም የለምጽ ደጅ ድል ነሣ። የንዳድ ደጅ ድል ነሣ።

ተፈጥሮን ሁሉ እንዲታዘዘው አድርጓል። እርሱ የአብርሃም ዘር፡ የንጉሣዊ ዘር፡ የተሰፋው ቃል የተገባለት፥ አብርሃምና፡ እርሱን የተከተለው ዘር ሁሉ፡ እስከ ንጉሳዊው ዘር ድረስ፡ እንዲሁም ከእርሱ በኋላ የመጣው ዘር ሁሉ ለእርሱ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እውነት ነው። በሽታን ድል ነሣ።

ፈተናን ድል ነሣ። ጠላት ፊቱ ላይ ሲተፋበት፡ መንጋጋውን ሲመታ፡ ሌላኛውን ጎኑን አዞረ። ከፊቱ ፂም ነቅለው ሲተፋበት፡ በፍጹም አልተሳደበም። የፈተናውን ደጅ ድል ነሥቶ ወረሰው።

48 እናንተም "ፈታኜ ይህን እንዳደርግ አይፈቅድልኝም፡" ብላችኋል። እናንተ፡ የአብርሃም ዘር ሆይ፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ እርሱ ስለ እናንተ ድል ነሥቶላችኋል።

49 በሰደቡት ጊዜ፡ መልሶ አልሰደባቸውም። በተሳለቁበት ጊዜ፡ ዝም አለ። ዲያብሎስ ነህ በተባለ ጊዜ፡ ዝም አለ። ስራው አንድ ነበረች፡ የአብን ስራ መስራት ነው፡ እርሱም ያንን ለማድረግ ወጣ። ከዚያም፡ በመጨረሻ፡ ወደ መስቀል ወሰዱት። ሞት እሱን መጋፈጥ ነበረበት። ሌሎቹ ሁሉ ባህሮችን ድል አደረጉ፡ ተፈጥሮን ድል ነሡ፡ አንበሶችን አሸነፉ፡ እሳትንም ድል ነሱ። ከሞት በስተቀር ሁሉንም ነገር አሸንፈዋል። እነሆ አንዱ ግን ነበረ፡ በዚያ፡ በደም ስሮቹ መካከል፡ ሞትን ድል የሚነሳበት ኃይል እየመታ መጣ። እጆቹንም ይዘው ዘርግተው በመስቀል ላይ ቸነከሩት። ደበደቡት አጥንቶቹም እስኪያዩት ድረስ ገፈፉት። ይህን ባደረጉ ጊዜ፡ ሌላም ሁሉ ባደረጉ ጊዜ፡ ሞት መታው፡ እንዲህም አለው፡ "ኢያሱን እንደገደልኩት አንተንም እገድልሃለሁ። ዳንኤልን እንደገደልኩት እገድልሃለሁ። እንድትሞትም፡ ይሄን ሁሉ አደርግብሃለሁ።"

50 ፀሐይም በራሷ እስክታፍር ድረስ ሞተ። ተፈጥሮ እስክታፍር እና መስራት እስኪያቅታት ድረስ ሞተ። እኩለ ቀን ላይ ፀሐይ ጠለቀች። ኮከቦቹ መውጣት አቃታቸው። ከቀኑ መኃል ላይ፡ ከፊታችሁ ያለውን እጃችሁን ማየት እስኪሳናችሁ

ድረስ ንጥረ ነገሮች ሁሉ ድቅድቅ ጨለማ እስኪሆኑ ድረስ ሞተ። ተፈጥሮም “ከእርሱ ጋር ልሙት፡” ያለች ይመለኛል።

51 ወንድሜ ሆይ! ዲያብሎስ የተወደደች ነፍሱን ወደ ሲኦል ወደ ታችኛው ክፍል አወረደው። በዚያም ደጆች ተከፈቱ፡ ከሶስት ቀን በኋላ ግን፡ ድል ነሣ። ኣሜን። “ዘሩ የጠላትን ደጅ ይወርሳል።” ሞትን አሸንፏል! ሲኦልን ድል አደረገ። በዚያ ትንሳኤ በፊተኛው ማለዳ፡ መቃብርን ድል አደረገ። አሁን በወደደን በእርሱ፡ ከአሸናፊዎች በላይ፡ እንበልጣለን።

52 በአሕዛብ በኩል የተሰፋውን ዘር ለማውጣት፡ ለማስቀጠልም፡ በጰንጤቆስጤ ዕለት፡ መንፈስ ቅዱስን ላከ። ይህም የተናቁ-የነበሩትን፡ አሕዛብን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይሰጣቸው ዘንድ፡ ወደ ተሰፋ ቃሉ ያመጣቸው ዘንድ ነው። አሁን ሁሉንም በሽታዎች የማሸነፍ መብት አለን። እሱ አስቀድሞ ድል ነስቷልና፡ እኛ ድል መንሣት አይጠበቅብንም። የገባውን ቃል በመቀበል ብቻ ሄደን መውረስ አለብን። አስቀድሞ ድል ተደርጓል። ሞት ተሸንፏል። ሲኦል ተሸንፏል። በሽታ ተሸንፏል። ፈተና ተሸንፏል። አጋንንቶች ሁሉ ተሸንፈዋል። ሲኦል ተሸንፏል። ሞት ተሸንፏል። መቃብር ተሸንፏል። እኛ ደጅ ላይ ቆመን፡ እንማርካለን፡ ጥይት መተኮስ አይጠበቅብንም። አስቀድሞ ተከፍሎልናልና።

53 የጠላቱ፡ የጠላቱን ደጅ ይወርሳል። ስንት ናቸው? በእልፍ የሚቆጠሩ አእላፋት፥ የጠላቱን ደጅ ሁሉ፡ የጠላቱን ሁሉ ይወርሳል። ከሞት ተነሳ። እኛም እርሱ ስለ ሰጠን እንወርሰዋለን። ይህ ሁሉ ነጻ ስጦታ ነው፡ ከዚህ ሌላም፡ እርሱ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ ያሸነፋቸው ደጆች ሁሉ የእኛ ናቸው። በሽታን አሸነፈ፡ ደጁን ወረሰ። እኛ ማድረግ ያለብን ብቸኛው ነገር፡ “ድል ነሺ በሆነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም!” እያልን ወደ ደጁ መሄድ ነው፡ ኣሜን።

54 የሞት ሰዓት በደረሰች ጊዜ፡ ሞትም “ተመልከቱኝ ሃይማኖቱን እንዲክድ አደርገዋለሁ፡” ይላል።

55 “በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ዮርዳኖስ ሆይ፡ ቁም!” የአብርሃም ዘር ደጁን ይወርሳል።

56 ለምን፡ ጳውሎስ፡ አንገቱን ሊቆርጡት በተዘጋጁ ጊዜ፡ የብርሃም ዘር ነውና፡ እንዲህ አለ፡ “ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፡ ድል መንሳትህ የት አለ? በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን የሰጠን እግዚአብሔር ይመስገን።”

57 የጠላቱን ደጅ ይወርሳል፡ ይማርካል። አሁን፡ ደጅ ላይ አልተቀጠቀጠም፡ ድል ነስቶ ይማርካል። ይወርሳል። ይህም በገዛ ስልጣኑ ነው።

58 በህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ሁሉንም በሽታዎች የመፈወስ ስልጣን ተቀምጧል። በሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁሉንም ፈተናዎች የማሸነፍ ስልጣን ተቀምጧል። በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ርስት ውስጥ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ኃጢአትን የማስር እና አሽቀንጥሮ የመጣል ስልጣን ተቀምጧል፡ ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀበሉ።

“የፈለጋችሁትን ሁሉ፡ በስሜ ለምኑ፡ ይሰጣችሁማል። ጥቂት ጊዜ አለ፡ አለምም (ዘር-ያልሆነው፡ ያልታደሰው ዘር) ከእንግዲህ አያየኝም። እናንተ ግን

ታዩኛላችሁ፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም አድራለሁ።" ምን? የንጉሳዊው ዘር። "እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እናንተም ታደርጋላችሁ። እኔ ከእናንተ ጋር መሆኔን አሳያለሁ፡ የሚያምኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋልና።"

የጠላቱን ዘር ይወርሳል። ይወርሳል። ደጁ ምንም ቢሆን፡ ዘሩ የጠላቶቹን ደጅ ይወርሳል። በሽታ፡ ፈተናዎች፡ ኃጢያት፡ የትኛውም ደጅ ቢሆን፡ ተሸንፏል። የአብርሃምም ዘር ይወርሰዋል።

59 ዛሬ ጠዋት፡ እኛ አሁን ከአሸናፊዎች በላይ፡ መሆናችንን በማወቃችሁ ደስ አይላችሁምን? ከአሸናፊዎችም በላይ! ኦህ፡ ምንም ልንዋጋ የሚገባን ነገር የለም። ትግሉ አልቋል። ፊሽካው ተነፍቷል። ሰንደቅ ዓላማው ቆሟል። እና በእያንዳንዱ የኃጢአት ኮረብታ መካከል፡ በእያንዳንዱ የታመመ ክፍል መካከል፡ ድል-አድራጊ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተቀመጠ፡ ወጣ ገባ መስቀል አለ። እኛ የምናደርገው ብቸኛው ነገር ማመን፣ መመልከት እና መኖር ነው።

"ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። አረጋግጣለሁ። በመጨረሻው ዘመን፡ 'ኦህ፡ ያ፡ ድሮ **ነበር**፡' የሚሉ ይመጣሉ። እኔ ግን ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። በዚህ ምድር፡ ያደረግኋቸውን ነገሮች፡ በውስጣችሁ ሆኜ፡ ተመሳሳይ ነገሮችን አደርጋለሁ። ያን ጊዜ ያውቃሉ። ያዩኛል። እ... ህዝቦቼ ያዩኛል። የአብርሃም ዘር ያየኛል። እነሱም ያውቁኛል። ያስታውሱኛል። ሌሎቹም፡ ያኔ እንዳደረጉት 'ብዔል ዘቡብ፡' ይሉኛል። እናንተ ግን ታውቁኛላችሁ፡ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁና። በዓይናችሁም፡ ታዩኛላችሁ። ታዩኛላችሁ፡ ምክንያቱም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁና፡ ያኔ ያደርግኳቸውን ነገሮች አደርጋቸዋለሁ። በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡ ያንኑ ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል።"

60 እናም፡ ዛሬ፡ የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ድል አድራጊውን፡ ከሙታን የተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ፡ ቆሞ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እየኖረ፡ በዚያ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ፡ የመቆም እና የማየት እድል አላት። ያኔ የጠላቶችን ሁሉ በር እንይዛለን።

61 እንግዲህ፡ ወንድሜ ሆይ፥ ዛሬ ጥዋት፡ ጠላት ካለህ፡ አንተ የአብርሃም ዘር ከሆንህ፡ ይህን ከሰማህ በኋላ፡ ያን ደጅ ከፊትህ የሚዘጋ በቂ አጋንንት በገሃነም ውስጥ አይኖርም። ይከፈታል። ምንም ቢሆን አይገደኝም። እንደ ተሰፋ ቃል ዘር፡ ቅረብና፡ እንዲህ በል፡ "ይህን የእኔ። ይህ የእኔ ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደሚያስነሳው ምሏል፡ እኔም፡ በኢየሱስ አማካኝነት፡ ድል አደርገዋለሁ። በአሸናፊው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እመጣለሁ። እያለፍኩ ነውና፡ ዞር በል።" ኣሜን። "የጠላትን ደጅ ይወርሳል።" ከዚያም በጌታ በኢየሱስ ደም ተሸፍናችሁ፡ ትከሻችሁን ቀጥ አድርጋችሁ፡ ጋሻችሁን እያብረቀረቀ ቁሙ። ጠላት ያንን እውቅና ይሰጠዋል።

62 እናንተ ዛሬ ጠዋት፡ እዚህ ያላችሁ፡ ልመና ካላችሁ፡ ራሶቻችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ አሁን በጸሎት ጊዜ እርሱን አነጋግሩት። ልመና ካለህ፡ እጅህን በኢየሱስ ፊት ከፍ ለማድረግ ፈቃደኛ ትሆነላህ? እናም በቃ በልባችሁ፡ በልብ ተናገሩ፡ እና፡ "ጌታ ሆይ፡ የሚያስፈልገኝን አንተ ታውቃለህ። አሁን፡ ዛሬ ጠዋት፡

ሰምቻለሁ፡ ያም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ 'የጠላትን ደጅ ይወርሳል።' ደጁን ለመውረስ መጣሁ። ምናልባት መጥፎ ቁጣ ያለኝ ይሆናል። ምናልባት መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገኛል። ኃጢአት አስሮኛል። ልመና አለኝ። አሁን ግን ወደ ደጁ እየደረስኩ ነው። ዛሬ ጠዋት፡ ደጄን፡ እወርሳለሁ። እንግዲያውስ፡ እየመጣሁ ነውና፡ መንገድ ክፈት።"

63 የተባረከ ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ሁሉ እጆች አይተሃል። ጌታ ሆይ፡ ይህ ቃልህ እንደሆነ አንተ ታውቃለህ። እኔ የጠቀስኩት፡ ከመጽሀፍ ቅዱስ ቃላት ውስጥ አመጣሁት። በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ገጸ ባህርያት፡ መንግስታትን ድል ነስተው ጽድቅን አመጡ፡ እሳትን እና፡ የእሳትን ኃይል አጠፉ፡ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፡ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፡ እናም፡ ኦህ፡ ከዚህም በላይ፡ ሴቶች ሙታኖቻቸውን በህይወት ተቀበሉ፡ እና ሌሎች ነገሮችም እንዲሁ፡ ቃል ገብተሃልና። ቃል ኪዳንህ ነው፡ "ዘሩ።" "ዘርህ፡ አብርሃም፡ የጠላትን ደጅ ይወርሳል።" ቃልህንም ጠበቀሃል።

64 አሁንም አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ የልባቸውን ሁሉ መሻት ስጣቸው። ከዚህም የተለዩ ሰዎች ሆነው ይሂዱ። ንጉሣዊው ዘር አሸንፎላቸዋልና፡ አሸናፊዎች መሆናቸውን—አውቀው፡ ይውጡ። ልዑሉ ንጉሥ፡ ከድንግል ተወልዶ፡ በመጣ ጊዜ፡ ጠላትን ሁሉ፡ እስከ ሞት ድረስ ድል አደረገ። ስለዚህ ሞት ራሱ የአብርሃምን ዘር ሊያስደነግጥ አይችልም። ምድርን እንደምናወርስ እና፡ በሚበልጥ ክብር፡ በክብር አካል እንደምንመለስ የተሰፋ ቃል አለን፡ ይህም የሚሆነው የመጨረሻው ጠላት፡ ወደ መንግስቱ በሚገባ ብቸኛው እና የመጨረሻው የእግዚአብሔር ልጅ እግር ስር ከወደቀ በኋላ ነው።

65 እጆቻቸውን ወደ ላይ ያደረጉ ካሉ፡ ጌታ ሆይ፡ ኃጢአተኞችን፡ አድናቸው። ባክ አድርገው የወደቁትም፡ ወድቀው መቅረት እንደሌለባቸው ያውቁ ዘንድ አሳውቃቸው። ባክ አርጎ የወደቀው ደጅም መውረስ ይችላል። ምናልባትም ቁጡ የሆነው፡ ክ—ክፉ ቃል ተናጋሪ፡ ክፉ አንደበትም፡ ወይም ፍትወት የተሞላ ልብ ያለው፡ ወይም ገንዘብን የሚመኝ፡ ስግብግብ፡ ወ—ወይም ክፉ ነገር የሚመኙ ሁሉ፡ ያንን ደጅ መውረስ እንደሚችሉ አሳውቃቸው። ምናልባት ጌታ ሆይ፡ በሽታ፡ ደዌም ቢሆን። ደጁን መውረስ ይችላሉ፡ "እርሱ ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ። የሰላማችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፡ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።" ዛሬ ጥዋት አሸናፊዎች ነን። አድርግልን፡ ጌታ ሆይ።

ከዚያ ሁሉ በተጨማሪም፡ ያ በእርሱ የተደረገው ታላቅ ስራ፡ እርሱ አሁንም ከእኛ ጋር ነው። አሁንም፡ እንደሚያደርገው ቃል ገብቷል። "ጥቂት ጊዜ አለ ዓለምም ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም እኖራለሁና።" አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ እራስህን ለእያንዳንዳቸው ታስተዋውቅ ዘንድ፡ እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም ጠየቅን። ኣሜን።

66 እውነት ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? በልባችሁ ውስጥ አንድም ሳትጠራጠሩ፡ እውነት እንደሆነ በጽኑ እመኑ። አሁን ይህንን አስታውሱ። የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በጣም ቀላል ከመሆኑ የተነሳ የአዋቂዎችን አእምሮን ያደናቅፋል። እስካሁን ካየኋቸው በጣም ቀላል ነገሮች... መንፈስ ቅዱስ ይህን ሲያደርግ አይቻለሁ። አንዳንዴ፡ እንደዚያ ስለመሆኑ ፈጽሜ

ያላሰብኳቸው ነገሮች፡ እናገራለሁ። አእምሮዬን ልጠቀም ብል፡ እኔም “አይ፡ ይህ ሊሆን አይችልም፡” እል ነበር። ይሁን እንጂ ዘወትር ትክክል ነው። እሱ ነገሮችን በቀላሉ ያደርጋል። ነገሮችን ሲያደርግ ራሱንም ለሕዝቡ ለማስታወቅ ያደርጋል። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ነው። እሱ በህዝቡ መካከል ነው። እሱ ይወዳቸዋል። እነርሱንም ሊሰራላቸው፡ እንዲሁም **የሚያደርገውን** ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን **ያደረገውን**፡ እንዲያውቁ፡ ሊረዳቸው ይፈልጋል። እሱ አስቀድሞ ሠርቷል። የእናንተ ነው። የራሳችሁ ነው። ከእግዚአብሔር ከአባታችን፡ ለቤተክርስቲያኑ የተሰጠ ነጻ ስጦታ ነው።

67 አሁንም ይህ ለባለ አእምሮዎች እጅግ አይዋጥላቸውም፡ እንደ ዳንኤል ዘመን፡ እንደ ብላቴኖችም ዕብራውያን ዘመን፡ እ—እና ዛሬ ጠዋት እንደ ተነጋገርንባቸው ሌሎችም ችምር ይከብዳቸዋል። አያችሁ፡ በዚያ ዘመን የነበረው ታላቁ የባለ አእምሮው አለም አሁን እንዳለ ለማሸነፍ አስቸጋሪ ነበር። ሁሌም ጠላት ነው፡ በገዛ እይታቸው ላይ፡ እና በገዛ ዘመናዊው ሳይንሳቸው እና ሌሎች ነገሮቻቸው፡ ያኔም ለአእምሮአቸው፡ ውስብስብ እንደነበረ ሁሉ፡ ዛሬም በእኛ እንዲሁ ነው። እዩት፡ ተመሳሳይ ነበር። ነገር ግን ሁል ጊዜ፡ ቆመው የሚደፍሩ፡ እና “እግዚአብሔር ትክክል ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው፡” በማለት የሚናገሩ ግን ነበሩ።

68 እና፡ እናንተም፡ እርሱ ራሱ ድል ነስቷልና፡ ድል መንሳት ከእናንተ አይጠበቅም። ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር ወጥታችሁ መውረስ ነው፡ ደጁ ላይ ቆማችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ “የእኔ ነው። ይህ የእኔ ነው። መዳኔን፡ እግዚአብሔር ሰጠኝ። መንፈስ ቅዱስን ብፈልግ፡ እግዚአብሔር ሰጠኝ። የተሰፋው ቃል ለእኔ፡ ለልጆቻችን፡ ጌታ ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው።” የቆምኩትም ለዚህ ነው። ልክ...

69 ይህ የተሰወረውን የማንበብ እና ሌላ፡ አገልግሎቴ ሁሉ፡ አሁን በቅርቡ ያበቃል። ኦህ፡ ሁሌም በቦታው ይሆናል። ይሁን እንጂ ከዚህ ወደሚበልጥ ታላቅ ነገር ስለሚሸጋገር፡ ይሄኛው በቅርብ ያበቃል። አያችሁ? ወደ ላይ እይወጣ ነው፥ እጅን ከመያዝ አንስቶ፡ የተሰወረውን እስከማንበብ ደረሰ፡ አሁንም ሌላኛው ለማድረግ እየተዘጋጀች ነው። አያችሁ? እዩት። ተመልከቱት እና እውነት ስለመሆኑ ተረዱ። አያችሁ? እውነት እንደሆነ እኔ አውቀዋለሁ። እነሆም ታላቅ ይሆናል፡ ከፍ ይላል፡ የተሻለ ይሆናል። በትክክል። ለምን፡ ቃል ስለገባ። እርሱ የገባውን ቃል ሁሉ፡ ያደርገዋል። ቃል ኪዳኑን አይዘነጋም። ይህስ ምንድነው? ከእኛ ጋር የሚኖረው-ህያው መገኘቱ፡ እንድናውቀው፡ ደጁን ስለእናንተ እንደወረሰላችሁ እንዲያሳውቃችሁ ነው።

70 እሱ የንጉሣዊ ዘር ነበር። እነዚያን በሮች ከእርሱ በቀር ማንም ሊያሸንፍ አይችልም። ከኋላ የነበሩት ሁሉ የእርሱ መምጣት ጥላዎች ነበሩ። እርሱ ሲመጣ ግን፡ ጦርነቱን ሁሉ ጨረሰ። ጦርነቱ በጌቴሴማኒ እና በቀራንዮ ተጠናቀቀ። አሁንም እንደ አሸናፊዎች፡ ቆመናል። እኛ የምንታገለው ሰልፍ የለም። እ... ትግሉ አልቋል። አሸንፈነዋል፡ የይዞታው መዝገብ አለን። በአባታችን፡ በእግዚአብሔር በራሱ የተጻፈ ዋስትና አለን፡ እርሱም እጁን አንስቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ዘሩ የጠላትን ደጅ ይወርሳል ብዬ በራሴ ምያለሁ።” ይኸው ነው። ቀድሞ የተወሰደ ነው። “እርሱ ስለ በደላችን **ቆሰሏል**። በእርሱ ቁስል እኛ **ተፈወስን**።” ቀድሞውኑ ተከናውኗል። ያለቀለት ስራ ነው። ወርሰነዋል። “እኔ የማደርገውን

ሥራ፡ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ዛሬ ጠዋት፡ ንጉሱ ከእኛ ጋር ነው። ታላቅ በረከቱ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በእኛ ላይ ይንቀሳቀሳል። ያንን የከበረ ስሜት ለማጣጣም፡ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት... ሰፍራው ላይ መሆኑ ለማወቅ። ያንን ለማወቅ እንዲህ ያለ አስደናቂ ማጽናኛ ሰጠን—ይህም እግዚአብሔር አባታችን መሆኑ ነው።

71 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት የጸሎት ካርዶችን የ—የሰጠ ይመስለኛል፡ ሰጥቷል አይደል? እንግዲህ፡ ነግሬዋለሁ፡ ከተበርናክሉ አባላት በስተቀር ሌሎች ሰዎች የማይመጡ ከሆነ፡ የጸሎት ካርዶችን አትስጥ፡ ብዬዋለሁ። ቢያንስ አስር፡ አስራ አምስት ሰዎች፡ ወይም የሆነ ነገር፡ እንግዶች ካ—ካሉ ግን፡ የጸሎት ካርዶችን ይስጣቸው፡ ምክንያቱም፡ ወደዚህ አምጥተን እንጸልይላቸው። ዛሬ ጠዋት ከእኛ ጋር ስንት እንግዶች አሉ? እጃችሁን አንሱ። ኦህ፡ ማይ! በእርግጠኝነት። አስራ አምስት ወይም ሃያ ይሆናሉ። በጣም ጥሩ። እነዚህን የጸሎት ካርዶች በመስመር ላይ እናስቀምጣቸዋለን እና ወደ መድረክ እናመጣቸዋለን። አያችሁ፡ "የተበርናክሉ" ሰዎች ያልኩበት ምክንያት፡ እዚህ ስላሉ ነው።

72 ይህ የተሰወረውን የመለየት ጸጋ፡ አስታውሱ፡ እንዲህ እያልኩ ነው፡ የተሰወረውን የመለየት ጸጋ ማብቂያው ቅርብ ነው፡ በጣም ትልቅ እና በጣም የተሻለ ነገር ይመጣል፡ እሱም በመንገድ ላይ ነው። እንዲህ ሆነ፡ ይህ ሲሆን፡ ትናንትና ከእኔ ጋር ቆመው የነበሩትን፡ ሁለቱ ወንድማማቾች፡ እንደነበሩ አውቃለሁ፡ አያችሁ፡ ከትላንት ወዲያም እንዲሁ፡ ይህ ሆነ። ይህ ሲሆን፡ አሁን፡ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ሆነ፡ ይህም አሁን በደጅ እንደቀረበ ማረጋገጫው ነው፡ አያችሁ፡ ሊፈጸም እየተዘጋጀ ነው።

73 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ አምላክ ነህ፡ እኛም ባሪያዎችህ ነን። ልባችንን ስለ ባረከው፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ፡ ስለ ቃልህ እናመሰግንሃለን። አሁንም ደስ ብሎናል። አሸናፊዎች መሆናችንን እያወቅን፡ እዚህ ተቀምጠናል። የጠላትን በሮች ሁሉ አስቀድመን ይዘናል። ለእኛ ተሰጥቶናል፡ እና ማስተር ቁልፍ በእጃችን አለ። የኢየሱስ ክርስቶስ ስም-... የጠላትን በር ሁሉ ይከፍታል። የኢየሱስን ስም ቁልፍ የሆነውን፡ ይህን ቁልፍ ውሰዱ፡ እና ያሰራችሁትን እና ከማንኛውም ቃል የራቁትን የጠላት በር ሁሉ አ-... አስከፍቱ።

እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ በኢየሱስ ስም፡ ይህን ቁልፍ ይዘን፡ የታመሙትንና የተቸገሩትን ደጅ ለመክፈት መጥተናል። ምክንያቱም በ— በቃሉ፡ "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ። አዳዲስ ቋቋዎችን ይናገራሉ። እባቦችን ቢይዙ፡ ወይም የሚገድል ነገር ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም። እጃቸውን በታመሙ ሰዎች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።" እነዚያ ነገሮች እውነት መሆናቸውን እናውቃለን። እናም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ጌታ ሆይ፡ በቃሉ መገለጥ፡ ሥጋ እንደ ፈጠረና፡ በእኛም እንዳደረ ህዝብ ሁሉ ይህን ያውቁ ዘንድ አድርግልን፡ ያም፡ "እርሱ ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን" የሚለውን ለማየት ይችሉ ዘንድ ስጣቸው። ዛሬ ጠዋትም፡ ይህን ተቀብለው፡ ከህመሞቻቸው እና ደዌአቸው ሁሉ ይፈወሱ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

74 ቴዲ፡ ከቻልክ፡ በእርጋታ እና በዝግታ፡ **እመን ብቻ**፡ ተጫወትልን እባክህ።

ከምን? የጀመራችሁት ከአንድ ነው? የጸሎት ካርድ፡ ቁጥር አንድ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ፣ አሥር፣

ወይም የተገኘ ሁሉ። በጣም ጥሩ። ከቻላችሁ፡ በእርጋታ ተነሰታችሁ፡ በዚህ በኩል ሁኑ።

[አንድ ወንድም "ሰንት ጠራህ፡" አለ?—እርታዒ።] ኧረ? [አንድ ሰው አለ፡ "ያ ነው። ያ ነው።"] ሰለ...

እሺ እንመልከተው፡ ቁጥር አንድ፡ ቁጥር ሁለት። ካርድ ቁጥር አንድ ያለው ማነው? [አንድ ወንድም፡ "እኔ ነኝ" አለ።—እርታዒ።] እሺ። ቁጥር ሁለት። በጣም ጥሩ፡ ጌታዬ። ቁጥር ሦሰት፣ ቁጥር አራት፣ ቁጥር አምሰት፣ ቁጥር ሰድሰት፣ ቁጥር ሰባት፣ ቁጥር ሰምንት፣ ቁጥር ዘጠኝ፣ ቁጥር አሥር።

75 እነሱ እየመጡ እና እዚህ ቆመው ቦታቸውን ሲይዙ፡ ይህን ጥያቄ ለሌሎቹ መጠየቅ እፈልጋለሁ። ከዚህ ተበርናክል አባላት መካከል፡ የታመሙት ሰዎች፡ ሰንት ናቸው? የተበርናክሉ ሰዎች ሆይ፡ እጃችሁን አንሡ። አምሰት ገደማ... ወይም አራት፣ አምሰት፣ ሰድሰት፣ ሰባት፣ ሰምንት። ሰምንት ወይም ዘጠኝ እጆች። እዚህ በተብርናክሉ ውሰጥ፡ ከዚኢህ ተበርናክል ያልሆነ፡ እንግዳ ሆኖ ከእኛ ጋር የተገኘ ሰው ካለ፡ ምናልባትም አገልግሎቱ ከተጀመረ በኋላ የመጣ እና የጸሎት ካርድ ያልወሰደ ሰው አለ? እጅህን ታነሳለህ? ከዚህ ሌላ... እግዚአብሔርን የሚፈልግ፡ ወ—ወደዚህ ተበርናክል መጥቶ የማያውቅ። የዚህ ተበርናክል አባላት ያልሆናችሁ፡ እና—ነገር ግን የታመማችሁ እና የጸሎት ካርድ የሌላችሁ፡ እና በጸሎት መታወሰ የምትፈልጉ አላችሁ? ሁሉም ሰው፡ እጃችሁን ማንሳት ትችላላችሁን? በጣም ጥሩ። መልካም። በጣም ጥሩ።

76 አሁን ለ—ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፡ በተቻላችሁ በትሕትና እንድትጠብቁ እጠይቃለሁ፡ እና ከዚያ ወዲያውኑ እንጀምራለን እና እንጀምረዋለን። እንግዲህ እንመልከተው። ቢሊ፡ የቀረ ቦታ አለህ'ዴ? እሺ። ቁጥር አሰር በዚያ ተገኝቷል? ከአንድ እሰከ አሰር ጠርቻለሁ።

አሥራ አንድ፣ አሥራ ሁለት፣ አሥራ ሦሰት፣ አሥራ አራት፣ አሥራ አምሰት፣ አሁን ቁሙ። ቁጥራቸው አሥር፣ አሥራ አንድ፣ አሥራ ሁለት፣ አሥራ ሦሰት፣ አሥራ አራት፣ አሥራ አምሰት ከሆኑ፣ ይቁሙ። እሺ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦሰት፣ አራት፣ አምሰት፣ ሰድሰት፣ ሰባት፣ ሰምንት፣ ዘጠኝ፣ አሥር፣ አሥራ አንድ፣ አሥራ ሁለት። ከአንድ እሰከ አሰራ አምሰት፡ የጎደሉ ሁለት አሉ። (... ? ... ሰባት፣ ሰምንት፣ ዘጠኝ፣ አሥር፣ አሥራ አንድ።) አሥራ አምሰት፣ አሥራ ሰድሰት፣ አሥራ ሰባት፣ አሥራ ሰምንት፣ አሥራ ዘጠኝ፣ ሃያ።

77 ኦህ፡ ቆይ አንዴ። የተበርናክሉ አባላት ላልሆኑ ሰዎች የጸሎት ካርድ ሰጥ አ—አልኩት። ትክክል። አያችሁ? ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ የመለየት ጸጋ፡ ሰለሚሆን ነው። ሰዎችም "እነዚህ ሰዎች ወደ ተበርናክሉ የሚመጡ ናቸው፡" ይላሉ። አያችሁ? ነ—ነግሬአችኋለሁ። እዚህ መጥታችሁ የማታውቁ... በጭራሽ መጥታችሁ የማታውቁ ሰንቶች አላችሁ? እሰኪ እጅህን እነይ፡ ከዚህ በፊት እኔ በማደርጋቸው ሰብሰባዎች ተገኝቶ የማያውቅ ሰው። በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ።

አሁን፡ በጣም ጥሩ፡ አንዴ አቁምልን፡ ወንድም ቴዲ።

78 አሁን ምናልባት እንዲህ እላለሁ፡ ይህም፡ ሁላችሁም ሰለ ሰብሰባዎቹ፡ እንዴት እንደሚካሄዱ፡ ሁሉ፡ ሰምታችኋል፡ በሰብሰባዎች የተገኛችሁ ሁሉ ሰምታችኋል ብዬ እገምታለሁ? አያችሁ? ጌታችን ኢየሱሰ በምድር ሳለ፡ ፈዋሽ

ነኝ አላለም። በእርግጥ፡ እርሱ የአብርሃም ዘር ነበር፡ እርሱም ጋር የተሰፋ ቃል ነበረው። አብ ካላሳየው በቀር ምንም እንደማያደርግ ተናግሯል። አይደል? እርሱም "አብ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እስካሳየኝ ድረስ ምንም ማድረግ አልችልም፡" ብሏል። ያየውም በ... "አብ **እስኪነግረኝ** ድረስ" ዝም። "አብ **እስካሳየኝ** ድረስ።" ቅዱስ ዮሐንስ 5፡19 ላይ፡ "አብ ሲያደርግ የማየው፡ ልጅም እንዲሁ ያደርጋል።"

79 አሁን እሱ በ—በመጣ ጊዜ፡ በአገልግሎቱ መጀመሪያ፡ እንዲህ ሲሆን አይተናል፡ እሱ የዳዊት ዙፋን—ከወረሰ በኋላ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] በመንፈሳዊ አነጋገር፡ የ...

የዮሐንስ ጥምቀት ላይ፡ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ በመጣ ጊዜ፡ እናም እሱ የተቀባ መሲሕ ሆነ። አሁን፡ እርሱ ሲወለድ የእግዚአብሔር ልጅ እንደነበር፡ አስታውሱ። የእግዚአብሔር በድንግልና-የተወለደ ልጅ ነበር። እሱ መሲሕ የሆነው ግን፡ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ በመጣ ጊዜ ነው፡ ምክንያቱም **መሲሕ** ማለት "የተቀባው" ማለት ነው። አያችሁ? መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ በወረደ ጊዜ እርሱ የተቀባ ሆነ። **በግ እና ርግብ** ብዬ ስሰብክ ሰምታችሁኛል። ከዚያም እንዳየነው፡ ከ... ከአርባ ቀናት ፈተናዎቹ በኋላ፡ እነሆ ወጣ።

80 አገልግሎቱስ እንዴት ተጀመረ፡ እንዴትስ ተጠናቀቀ? በአገልግሎቱ ውስጥ እንድርያስ የሚባል አንድ ሰው፡ እናገኛለን፡ እርሱም ሄዶ ወንድሙን፡ ስምዖንን፡ ዓሣ አጥማጅ፡ አግኝቶ ወደ ኢየሱስ አመጣው። ኢየሱስም፡ እንዲህ አለው፡ "ስምህ ስምኦን ይባላል። የአባትህ ስም ዮናስ ነው። ከአሁን ጀምሮ **ጴጥሮስ** ትባላለህ ትርጉሙም 'ትንሹ ድንጋይ፡' ማለት ነው።" ያንን ታስታውሳላችሁ? ይህ ሰው ኢየሱስ በነገረው ነገር በጣም ተገረመ!

አሁን፡ መሲሑ ይህን ማድረግ ነበረበት አይደል? ይሄን ሰንቶች ታውቃላችሁ፡ "ኣሜን፡" በሉ እስኪ። አምላክ-የሆነ ነቢይ መሆን ነበረበት። አዎን፡ ጌታዬ። ሙሴ እንዲህ አለ፡ "አምላክህ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣል። እንዲህም ይሆናል ይህን ነቢይ የማይሰማ ሁሉ ከህዝቡ መካከል ይጠፋል።"

81 አሁን፡ ከዚያ በኋላ፡ እንደተረዳነው፡ ወደ... "ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ።" እነማን ነበሩ? አይሁዶች፡ ከፍጥረታቸው። "የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፡" ስለዚህም በዚያ ምክንያት... አሁን ወደ አሕዛብ መሄድ ተገባው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም። "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ስለዚህ አሁን ወደ አህዛብ ዞሯል፡ እነሆም፡ ሁለት ሺህ ዓመታት ሆኖታል። አሁን ግን ያደረጋቸውን ነገሮች አስተውሉ።

82 ፊልጶስም፡ ይህን አይቶ፡ ናትናኤልን አግኝቶ፡ ለናትናኤልም ማን እንዳገኘውና ያደረገውን ነገረው። ያ ደግሞ አስገረመው። ማመን አልቻለም። በጌታ በኢየሱስ ፊት በመጣ ጊዜ ግን፡ ያለበትን ሰፍራ ባገኘ ጊዜ፥ ወደ ፊቱ ቀረበና፡ ኢየሱስ፡ "እነሆ ተንኰል የሌለበት እስራኤላዊ" አለው።

83 አሁን፡ እናንተ በዚያ ብትኖሩ ኖሮ፡ እሱ ማን እንደ ሆነ ለመረዳት በቂ መንፈሳዊነት ይኖረኝ ነበር ብላችሁ ታስባላችሁን? ያንን አደርጋለሁ ብላችሁ ታስባላችሁን? አሁን ተከታተሉ። አያችሁ? ያ ሰው፡ እንግዳ ነው፡ እ-... እና፡

ዓሣ አጥማጅ ሊሆን ይችላል። አናጺ ነበር፡ እንደዚያ ነበር። ይህ አናጺ ሰው፡ መካከለኛ-እድሜ የነበረው ሰው በዚያ ቆሟል። እነሆም ይህ ሰው መጣ። አየውና፡ ልክ እንደነዚያ ሰዎች፡ እንዲህ አለው፡ "እነሆ ተንኰል የሌለበት እስራኤላዊ።" እሺ፡ እስራኤላዊ መሆኑን እንዴት አወቀ? በአለባበሱ አይደለም፡ ምክንያቱም አለባበሳቸው የሁሉም አንድ ዓይነት ነው። "ተንኮል የሌለበት።" ተንኮል የ—የሌለበት ሰው መሆኑን እንዴት አወቀ?

84 ስለዚህ ይህን ሰው አስገረመው። እውነተኛ አማኝ ስለነበረ፡ እንዲህ አለ፡ "ረቢ፡" ወይም ወንድም፡ ሰባኪ፡ መምህር፡ "መቼ አየኸኝ? " እዩት፡ እየጠየቀው ነበር።

85 "ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ ከበለስ በታች ሳለህ፡ አየሁህ፡" አለው።

እንዲህም አለ፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ።"

86 ኢየሱስም፡ "ይህን ስለነገርኩህ አሁን አመንከኝ? አሁን ከዚህ የሚበልጡ ነገሮችን ታያለህ።"

87 እናም የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለች ብዬ የማምንበት ምክንያት ይህ ነው። በቅርቡ ወደዚያ ለመግባት ዝግጅት ላይ ናቸው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም አምነውታልና። በህይማኖት ተቋማት ምክንያት፡ ያልተቀበሉት፡ ምንም ነገር ማመናቸው ያጠራጥረኛል። አያችሁ? በነገሮች... በብርሃን ትሄዳለህ ወይም ትታወራለህ። ብርሃን ያሳውራል፡ ወይም መንገድ ያሳያል።

88 በነጻነት ሐውልት፡ ትናንሽ ወፎችን፡ አየሁ። አየህ፡ ወንድም ቶምሰ፡ ወደዚያ ስትሄድ፡ እነዚያን ሳታያቸው እንዳትቀር። በዚያም እሰኪሞቱ ድረሰ ጭንቅላታቸውን፡ ያጋጩ ነበር። እኔም "ለምንድን ነው፡" አልኩኝ?

89 እንዲህ አልኩኝ፡ "በአውሎ ነፋሱ ወቅት፡ ሰለደህንነታቸው፡ ብርሃኑን እንደመከተል፡ መብራቱን ለማጥፋት ይሞክራሉ። እራሳቸውን ይገድላሉ።"

90 ከብርሃን ጋር ሰትዋጉ፡ የምታተርፉት ብቸኛው ነገር፡ እራሰህን፡ መንፈሳዊ ጥፋት ማጥፋት ብቻ ነው። እርሱ በብርሃን እንዳለ ብቻ በብርሃን ተመላለሱ፡ ያን ጊዜ እርሰ በርሳችን ኅብረት ይኖረናል፡ አብያተ ክርሰቲያናት ሁሉም በእምነት ወደፊት ይቀጥላሉ የእግዚአብሔርን በረከቶች ያገኛሉ። ያ ድንቅ አይሆንምን?

91 ሳምራዊቷ ሴት በመጣች ጊዜ ተመልከቱ። እሷ ሳምራዊት ናት፡ (አይሁዳዊት አይደለችም) ሳትሆን፡ ሳምራዊት ነበረች። እርሱም "የሚጠጣ ሰጪኝ፡" አላት። ንግግር ቀጠሉ።

ይህ አሁን ለአዳዲሰ እንግዶች ነው።

92 ንግግሩም ቀጠለ። አሁን፡ እርሱ መሲሕ ሰለመሆኑ ምንም አታውቅም። ተራ—ሰው፡ አይሁዳዊ ነበር። መጀመሪያ ምን እንደተናገረች አይታችኋል? "እንግዲህ፡ ለእናንተ ለአይሁድ ከሳምራዊት ሴት ጋር እንዲህ መነጋገር ለእናንተ ልማድ አይደለም፡" አለችው። "እርሰ በርሳችን አንግባባም፡" አለችው።

93 እርሱም፡- "ከማን ጋር እንደምትናገሪ ብታውቂ ግን፡ የሚጠጣ ትጠይቂኝ ነበርሽ አላት። እኔም ባመጣሁልሽ፡ ውኃም በሰጠሁሽ ነበር፡ አንቺም ለመቅዳት ወደዚህ ባልመጣሽ ነበር።"

94 ለምን፡ አለች፡ “ቆይ እስኪ አንድ ደቂቃ።” “በዚህ ተራራ እንሰግዳለን፡ እ—— እናንተም አይሁድ በኢየሩሳሌም ትሰግዳላችሁ፡” አለችው።

95 ኢየሱስም፡ “በመንፈስ እንጂ——በኢየሩሳሌምም ሆነ በዚህ ተራራ፡ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። እግዚአብሔር መንፈስ ነውና፡ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።” አያችሁ? እና፡ ቀጠለ፡ ችግሯ የት እንዳለ እስኪያውቅ ድረስ ንግግሩን ቀጠለ። እሺ፡ ችግሯ የት እንደነበረ ታውቃላችሁ? በውኃ ጉድጓዱ እየገብ የነበረችው ሴት ጉዳይ ምን እንደሆነ የሚያውቅ አለ? ብዙ ባሎች ነበሯት፡ አይደል? ስለዚህ እንዲህ አላት። “ባልሽን ይዘሽ ወደዚህ ነይ።”

“ምንም ባል የለኝም፡” አለችው።

96 አላትም፡ “ትክክል ነው። አምስት ነበሩሽ፡ አሁንም ከአንቺ ጋር ያለውም የአንቺ አይደለም።”

97 እሷም፡ “ጌታዬ!” አሁን ተመልከቷት። “ጌታዬ፡ ነብይ እንደሆንክ አያለሁ።”

የጠርዙን ንባብ በደንብ ካያችሁት፡ ይህ ትደርሱበታላችሁ። “ጌታዬ፡” በዋናው ላይ፡ “እንዲህ እንደሆንክ፡ አንተ **ያንን** ነብይ እንደሆንክ፡ አያለሁ።” አስታውሱ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በተደጋጋሚ፡ “ያ ነቢይ፡ አንተ ነህን ‘ያ ነቢይ? ” የትኛው ነብይ ነበር? ሙሴ ይነሣል ያለው።

“አንተ ነቢይ እንደሆንክ አይቻለሁ። አሁን፡ እኛ እንዲህ ተምረናል፡ መሲሑ ሲመጣ፡ እነዚህን ነገሮች እንደሚያደርግ እናውቃለን።” የመሲሑ ምልክት ያ ነበርና። ትክክል ነው? ችግሯ ምን እንደሆነ ለማወቅ። አለችም፡ “መሲሑ ሲመጣ፡ እነዚህን ነገሮች እንደሚነግረን እናውቃለን። አንተ ግን ማን ነህ? ”

እርሱም “ከአንቺ ጋር የምነጋገረው፡ እኔ እሱ ነኝ፡” አላት።

98 የውሃ ማሰሮዋን ትታ፡ ወደ ከተማ ሮጠች፡ ሳሰባት፡ ልቧን እንዲህ ደግፋ፡ እንዲህ እያለች፡ እጆቿን ደረቷ ላይ አድርጋ እየዘለለች፡ እንዲህ ያለች ይመስለኛል፡ “ያደረግሁትን የነገረኝን ሰው፡ ኑና እዩት። ይህ ራሱ መሲሕ አይደለምን? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመጣ የተናገረው እሱ አይደለምን? እዚያ ቁጭ ብሏል አይሁዳዊ ነው፡ ተራ ሰው፡ እናጺ ይመስላል። አምስት ባሎች እንደነበሩኝ ግን ነግሮኛል፡ እናንተም ሁላችሁ ይህ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ። ይህ መሲሕ መሆን አለበት።” ትክክል ነው?

99 አሁን፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “ትንሽ ጊዜ፡ ጥቂት ጊዜ አለ፡ ዓለም ከእንግዲህ አያየኝም። ሆኖም፡ እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በእናንተ ውስጥም እኖራለሁና፡ እናንተ ታዩኛላችሁ። እኔ የማደርገውን ሥራ ታደርጋላችሁ። እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፡ በመንፈስ መልክ እመለሳለሁና፡ እኔ እዚህ ካደረኩት በላይ፡ እናንተም ታደርጋላችሁ።”

መሰዋዕትነቱ ተከፍሏል። የንጉሥ ዘር ሞቷል፥ የንጉሥ ዘር እንደገና ተነስቷል። አሁን ቤተክርስቲያን ይህን በማመን፡ ጸድቃለች፡ እና የንጉሥ ዘር ወደ እነዚህ ሰዎች ሊመጣ አልፎ ተርፎም የጋራ ወራሾች፡ ወንድ እና ሴቶች ልጆች ሊያደርጋቸው ይችላል።

100 እንግዲህ፡ እዚህ ከጸሎት መስመር ውጭ፡ ላላችሁ እናንተ፡ ዛሬ ጠዋት ሰጠራው... ካርዶችን ለእነዚያ ብቻ እንዲሰጣቸው ነገርኩት። ደወለልኝ እና፡ እንዲህ አለ፡ "አባዬ፡ ወርደህ የጸሎት ካርድ መስጠት ትፈልጋለህ'ዴ? "

101 "ከተበርናክል ሰዎች ውጪ የሆኑ አሰር የሚያህሉ ሰዎች ከተገኙ ስጥ፡" አልኩት።

102 አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ በተበርናክል ውስጥ ጠርቼ የጸሎት ካርዶችን እሰጣቸዋለሁ። እናንተም እየተነሣችሁ፡ "እይ፡ ስለሚያውቃቸው ነው። ከዚህ ተበርናክል ናቸው። ሁኔታቸውን አስቀድሞ ያውቃል። ያለጥርጥር፡" ትላላላችሁ።

103 ከዚያም በተቃራኒውን አደርጋለሁ፡ እንዲህም አልኩኝ፡ "የተበርናክሉ ያልሆኑት ብቻ፡ ይምጡ። መልካም። እናንተ የተብርናክሉ አባላት ያልሆናችሁ፣ ወደ ጸሎት መስመር የምትመጡት እናንተ ትሆናላችሁ።"

104 ተበርናክሉም "ኡህ፡ አናውቃቸውም ነበር፡" ይላል። "ችግራቸው ምን እንደሆነ አናውቅም። ስለ ጉዳዩ እየዋሸ ሊሆን ይችላል።" አያችሁ?

105 ከዚያም አልኩኝ፡ "ማንም አይምጣ። መንፈስ ቅዱስ ከተበርናክሉ ያልሆኑትን በዚህ ውስጥ ያሉትን ብቻ ይምረጥ፡ ክከተቀመጡት መካከል ያምጣ።" አሁንም፡ እናንተ...

106 የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን አስቀድሞ ካልተወሰነ በቀር፡ ሰውን ወደ እግዚአብሔር የምታመጡበት፡ ምንም መንገድ የለም። ይህን ለማድረግ ምንም መንገድ የለም። ኢየሱስም፡ "አባቴ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም" አለ። እና እውነታው ይህ ነው። ምንም ቢያደርግ፡ ተቃዋሚው አለ። "**በዚህ** መንገድ ካደረገው፡ **በዚያ** መንገድ መሆን ነበረበት። እና **በዚህ** መንገድ፡ **በዚያ** መንገድ መሆን ነበረበት።" አያችሁ፡ በቃ አለማመን ነው። ጥበብ ግን በልጆቿ ትጸድቃለች። እንግዲያውስ፡ እናንተም፡ እዩ።

107 አሁን እዚህ ጋር፡ ለዚህ የሕዝብ ጉባኤ—ለማለት የሞከርኩ ያለሁት፡ ይህ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ያ የንጉሣዊ ዘር መሆኑ ነው። እኛ አይደለንም፥ እሱ ነው። እኛ የዚያ ወራሾች ነን፡ ሁሉም ነገር ግን የእኛ ነው። ስምዖን በመጣ በዚያ ቀን ብትኖሩስ? እና፡ እናንተም፡ ማናችሁም... እሱ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር ይህ ነው።

108 አሁን፡ እንግዲህ ካደረገ፡ ለእነዚህ ሰዎች የሚያደርግላቸው የመጀመሪያ ነገር ያ ይሆናል። ከዚህ በፊት አይተውት አያውቁምና።

109 ወረቀት ላይ ስሙን መፈረም የሚያስችል ትምህርት ያልነበረው፡ ምስኪኑ አሣ አጥማጅ፡ ስምኦን ግን መጣ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እሱ "መሃይም እና ያልተማረ" እንደነበረ ይናገራል። **እና** አገናኝ ነው። ሁለቱም፡ "መሃይምም እና ያልተማረም" ነበረ። ከዚያም በምልክት፡ በኃይል፡ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ... ኢየሱስ፡ ኢየሱስም አለው፡ "ስምህ 3ስምኦን ይባላል።" ምን ያስበ ይመስላችኋል? እዚያ ቆማችሁ ቢሆን ምን ታስቡ ነበር ይሆን? "የአባትህም ስም ዮናስ ነው። ከዛሬ ጀምሮ ጴጥሮስ ትባላለህ።" ምን—ምን ታስቡ ነበር ይሆን? ሰውየው እእምሮውን እያነበበ ነበርን? እሺ፡ ምን ታስቡ ነበር ይሆን? ይህ የመሲሑ ምልክት ነው ብላችሁ ታስቡ ነበር ይሆን?

110 ይህ በአንደኛው ዘመን የመሲሑ ምልክት ከነበረ፡ የመሲሑ ምልክት መሆኑ ይቀጥላል፡ ሁለተኛ ዘመን፣ ሦስተኛው፣ አራተኛው ዘመን ላይ። እያንዳንዱ ዘመን ላይ አንድ መሆን አለበት፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊለወጥ አይችልም። መሲሑ አምላክ መሆኑን የምታውቁ ሰንቶች ናችሁ? በእርግጠኝነት። የተቀባው ነበር። በእርግጠኝነት። ስለዚህ አይለወጥም። ያው መሆን አለበት።

111 በአይሁድ ላይ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር በሳምራውያን ላይ መመስከር ያለበት ለዚህ ነው። ምክንያቱም፡ ሦስቱ የሰው ዘር ሐረጎች ካም፣ ሴም፣ እና የያፌት ሰዎች ናቸው፥ አይሁድ፣ አሕዛብ፣ እና ሳምራውያን።

112 አሁን፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስተውላችኋል? ጴጥሮስ የመንግሥቱ ቁልፎች እንደነበረው የምታውቁት ሰንቶች ናችሁ? አስተውላችኋል? በበዓለ ኀምሣ ቀን፡ ለአይሁዶች ከፈተላቸው። ፊልጶስም ወርዶ ለሳምራውያን ሰበከላቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም አጠመቃቸው፡ መንፈስ ቅዱስ ግን በእነርሱ ላይ ገና አልወረደም ነበር። እና መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ፡ እጁን የጫነባቸውን ጴጥሮስን መላክ ነበረባቸው። ልክ ነው? እና የቆርኔሌዎስ ቤት ደግሞ፡ አ— አሕዛብ ተቀበሉት። ጉዳዩ ያ ነበር። ከዚያ ጊዜ ወዲህ፡ አሁን ለሁሉ ክፍት ሆናለች። ስለዚህ ይኸው ነው፡ እንግዲህ፡ መክፈት ነበረበት። እግዚአብሔር ነገሮችን የሚሰራበት መንገድ አለው።

113 አሁን፡ ዛሬ ጥዋት፡ ይህ ለዘሩ የገባውን ቃል የገባው፡ ዘሩም እዚህ ካለ... እያንዳንዳችሁ ዘር እንደሆናችሁ ማመን እፈልጋለሁ። ዘሩ እዚህ ተቀምጦ ካለ፡ በእርግጥ ዘሩ የተሰፋውን ቃል ያየዋል። አሁን፡ እዚህ የቆሙት እነዚህ ሁሉ፡ ከዚህ በፊት በእነዚህ ስብሰባዎች ተገኝተው እንደማያውቁ ለማሳየት እጃቸውን አውጥተዋል። ለእኔ እንግዳዎች ናቸው። ከመካከላቸው አንዱን አላውቅም። እንዲሁ እዚህ የመጡ። እና ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ቢሊ የጸሎት ካርድ ሰጣቸው፡ እነሆም እዚህ ቆመዋል። በክፍሉ ውስጥ ያላችሁ ብዙዎቻችሁም፡ የጸሎት ካርድ እንደሌላችሁ፡ እና እዚህ እንግዶች እንደሆናችሁ ለማሳየት እጆቻችሁን አንስታችኋል፡ አሁንም ለዚህ እንግዳ ነበራችሁ። ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። የተሰፋ ቃል ወራሾች እንደሆናችሁ ብቻ እመኑ። ብቻ በእርሱ ግርፋት እንደ ተፈወሳቹ እመኑ። በፍጹም ልባችሁም እመኑ፡ እና እርሱን ጠብቁት።

114 ይህ ስጦታ ብቸኛው ነገሩ፡ እራስህን ለእርሱ ማስገዛት ብቻ ነው። እኔ ምንም አልልም፡ ተናጋሪው ራሱ ነው። እንግዲህ የመንፈሱ ትንቢት ከሆነ፡ ነቢዩ ሁል ጊዜ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ይኖረዋል። ሁልጊዜም ትክክል ይሆናል። በዶክትሪኑ አትጠራጠሩ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሆነ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል። እግዚአብሔር አንድ ነገር ተናግሮ፡ እንደገና በሌላ መንገድ አያጣምመውም። ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነገር መሆን አለበት።

115 አሁን፡ እናንተ ሆይ፡ እመኑ። በውስጣችሁ ባለው ነገር ሁሉ፡ እመኑ። ከአሁን በኋላ ወዲያ ወዲህ አትንቀሳቀሱ። አሁን፡ ሁላችሁም በእርጋታ ተቀመጡ።

በተቻለ መጠን በቀስታ እና በዝግታ ይሁን።

ዛሬ ጠዋት፡ እዚህ የቆመው፡ የመጀመሪያው ሰው ወንድ ሆኗል። አሁን ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እናያለን።

116 አሁንስ በምን ላይ እንደቆምኩኝ ይታያችኋል? ይሄን ስንቶች ትረዱታላችሁ? እነሆም በህይወቴ፡ ዓይኖቼን ያላዩአቸው ወንዶች እና ሴቶች፡ እዚህ ቆመዋል። በስብሰባው ተገኝተው እያውቁም፡ በምን አይነት ሁኔታ እንደቆሙ ተመልከቱ። ምን እንደሚሆን እያውቁም። እኔም ምን እንደሚሆን አላውቅም። እግዚአብሔር ግን ቃል ገባ። አብርሃም ይስሐቅን ለመግደል ቢላውን ሲያወጣ ምን እንደሚሆን አላወቀም ነበር፡ እግዚአብሔር ግን ቃል ገባለት። አራት ነጥብ። ከሙታንም እንደሚያስነሣ አውቆ፡ ከሙታን እንደ እንዱ አድርጎ ተቀበለው። ልክ ነው? ስለዚህ አራት ነጥብ።

117 ስለዚህ፡ እነሆ ይህ ሰው አጠገቤ ቆሟል፡ አይቼው አላውቅም፡ ስለ እሱ ምንም የማውቀው ነገር የለም። እንዳችን ለሌላው እንግዳ ነን። አንተዋወቅም። እግዚአብሔር ሁለታችንንም ያውቃል።

አሁን፡ በመለኮታዊ ስጦታ፡ በዚህ ስጦታ እንዲህ ማድረግ ከቻልኩ... እንግዲህ፡ እነዚህ ስጦታዎች ከእናንተ ጋር የተውለዱ ናቸው። እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ወስኗቸዋል። ስንቶች ታውቃላችሁ? ይሄን ስጦታ ለማግኘት፡ ከእኔ የተነሣ አይደለም። የመረጠው እግዚአብሄር ነው። በጭራሽ እኔ አልመረጥኩትም። በሱ ምርጫ ነው። እያችሁ? እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት፡ እና የተለያዩ ሰዎች፡ ይህን ለማድረግ፡ አስቀድሞ ተወስነዋል።

118 አሁን፡ ሰውዬው ከታመመ፡ ልፈውሰው አልችልም። ሰውዬው የተቸገረ ከሆነ፡ እኔ ልረዳው እችላለው ወይስ አልችልም በሚል የተመረኮዘ ይሆናል። ምናልባት፡ እንደ እሱ ያለ ሌላ ነገር ከሆነ... እሱን ልረዳው የምችለው ትንሽ ነገር ቢሆን፡ እንግዲህ፡ ባደርገው ደስ ይለኛል። ምናልባት ቁጡ ይሆናል። ምናልባት ክርስቲያን አይደለም ይሆናል። ምናልባት ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። ምናልባት እሱ አስመሳይ ሊሆን ይችላል። አላውቅም። ሾልኮ የገባ፡ ድብቅ ጥቃት ቢሆንስ፡ እዚህ መጥቶ እራሱን እንደ አንድ ነገር ቢያደርግስ? የሚሆነውን ተመልከቱ፡ እዩ፡ ም—ምን እንደሚከሰት ብቻ ተመልከቱ። እኔ አላውቅም።

119 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ እዚህ ቆማችሁ፡ ከዚያም እግዚአብሔር ቃል እንደ ገባ አውቃችሁ፡ በፍጹም መቆም ከቻላችሁ፡ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ይፈጽማል። እያችሁ? አሁን፡ በዚህ መካከል፡ አሁን እዚህ ጋር፡ እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች የገባውን ቃል ኪዳን፡ የሚጠብቅ ከሆነ፥ እስኪ በዚያ ከተቀመጣችሁ መካከል፡ በሙሉ ልባችሁ የምታምኑ ስንቶች አላችሁ? በሙሉ ልባችሁ፡ ታምናላችሁን? እንግዲያውስ እመኑኝ።

120 እስኪ አሁን እንመልከተው። አንድ ቃል እንውሰድ። አሁን፡ ሰምዖን ጴጥሮስ ወደ ጌታ ኢየሱስ መጣ። ወደ ጌታ ኢየሱስም በደረሰ ጊዜ፡ ጌታ ኢየሱስ ማን እንደ ሆነ ነገረው፡ ስ—ስለ ህይወቱም ነገር ነገረው። እንግዲያውስ፡ ያንኑ ኢየሱስ ዛሬም ህያው ነው። እ... ከሙታን መነሣቱን ታምናላችሁን? የመሲሐዊ መንፈስ፡ ዛሬም፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ልክ እንደ ሁልጊዜው እንደሚኖር ታምናላችሁን? በጣም ጥሩ።

121 አሁን፡ እናንተ በጉባኤው ያላችሁ፡ የጸሎት ካርድ የሌላችሁ፡ በዚህ መንገድ ተመልክታችሁ፡ "ጌታ ሆይ" በሉት! እርግጥ ነው፡ በጉባኤው የጸሎት ካርድ የለም፡ ሁሉም እዚህ እንዲቆሙ አድርጌያለሁ። እናንተ በጉባኤው ያላችሁ፡

“ጌታ ሆይ፡ ዳሰሰኝ” በሉት። እና ምን እንደሚከሰት ጠብቁ። ምን እንደሚከሰት ጠብቁ... ? ...

122 አሁን፡ ወዳጄ ሆይ፡ በአለም ውስጥ አንተን የምረዳበት መንገድ ቢኖረኝ፡ አደርገው ነበር። ይኸውልህ፡ እኔ፡ ሁለታችንም እንግዳ ነን፡ እኔም አንተን—ለመጀምሪያ ጊዜ ማግኘቴ ነው። እኔ ግን እንደ አገልጋይ፡ እውነትን የመናገር፡ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር የመሆን ሀላፊነት አለብኝ። እና፡ አሁን፡ ምንም እንድትነግረኝ አልፈልግም። እውነት ነው ወይስ አይደለም እንድትመልስልኝ ብቻ እፈልጋለው፡ ከዚያም እሱ ራሱ ያደርገዋል። እና እዚህ መድረክ ላይ፡ በዚህ አካል በኩል፡ በኢየሱስ አካል በኩል ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ቢያደርግ!

ያም እግዚአብሔር፡ በክርስቶስ ነው። ኢየሱስም፡ “በእኔ ውስጥ ያለው አብ፡ እስኪያሳየኝ ድረስ፡ ምንም አላደርግም። ምን ማድረግ እንዳለብኝ እሱ ይነግረኛል።” ስለዚህ ለሴቲቱ የነገራት ኢየሱስ አልነበረም። አብ በእርሱ ነበር፡ ለሴቲቱ የነገራት። ስምዖን ጴጥሮስ ማን እንደ ሆነ ያወቀው ኢየሱስ—አልነበረምን፡ ስምዖን ጴጥሮስ ማን እንደ ሆነ ያወቀው፡ በእርሱ ውስጥ ያደረው አብ ነው። ያ ነው። አያችሁ? ያ ነው።

123 እንግዲያውስ፡ ዋዳጄ፡ ሞቅ አርጎ የ—የ—የሚቀበል የሚንቀሳቀስ መንፈስ አይብሃለሁና፡ አሁን፡ አንተ ክርስቲያን እንደሆንክ፡ መናገር እችላለሁ። እና፡ እሱ፡ አማኝ ነው። ክርስትያንም ነው። እና የሆድ ህመም በሚያነሣሣብህ በጭንቀት ህመም እየተሰቃየህ ትገኛለህ። ልክ ነው? [ያ ወንድም “ትክክል ነው፡” አለ።—አርታዒ።] አያችሁ? አያችሁ? እንግዲህ፡ ፍጹም ትክክል ነው። ይህ እንዴት ሆነ? ይህን ማወቅ እንዴት ቻልኩ? ይህ በምኔ ላውቀው ቻልኩ? ከዚህ በፊት ተያይተን እንኳን አናውቅም። እውነት ነው። አይደለም እንዴ? [“ልክ ነው።”] ምናልባት ስለ አንተ ሌላ ነገር ይነግርህ ይሆናል። እነግርሃለሁ። እንዲህ ነው። ከጎንህ አንድ ሴት አየሁ። ከአንተ ጋር ናት። ሚስትህ ናት። እሷም፡ እርዳታ ትፈልጋለች። አዎን፡ ጌታዬ። እግዚአብሔር የሚስትህ ችግር ምን እንደሆነ እዚህ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? [“እንደሚችል አውቃለሁ።”] እሺ፡ ጌታዬ። የልብ ችግር፡ ውስብስብ ችግሮች አጋጥሟታል። ትክክል ነው። አይደለም እንዴ? ጭንቀትም፡ እንዲሁ። አዎን፡ ጌታዬ። አሁን፡ አንተ ከዚህ ከተማ አይደለህም። ወደ ቤት ስትሄድ፡ **በዚህ** መንገድ ወደ ሲንሲናቲ ትመለሳለህ። ትክክል ነው። ከሲንሲናቲ፡ ኦሃዮ ነህ። ስምህ ሚሊከን ይባላል። ሂድ፡ ወደ ቤትህ ተመለስ፡ ደህናም ሁን። ጌታ ይባርክሃል፡ እናም አንተ እና ሚስትህ ትፈወሳላችሁ። እግዚአብሀር ይባርክህ።

ወዲህ ና፡ ወዳጄ። አንተስ ታምናለህ? እምነት ብቻ ይኑርህ። እንዳትጠራጠር።

124 በትክክል ትሑት ሁን። ሁላችሁም ትሑታን ሁኑ፡ በእርጋታ ጠብቁ። አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ እጅግ ስስ ነው። ስንቶች ታውቃላችሁ? መንፈስ ቅዱስ፡ እጅግ ስስ ነው፡ አያችሁ፡ ትንሽ ረብሻ ያደናቅፈዋል።

125 እንደ ዶክተሮች ገለጻ፡ በልብ ሕመም፡ ወዲያውኑ ትሞታለህ ብለውሃል። ትክክል ነው። ሚስተር ሞስሊ፡ አንተ የመጣኸው ከቺካጎ ነው። የመጀመሪያ ስምህ ቴዎዶር ይባላል። እግዚአብሔርን ታምናለህ? [ያ ወንድም “እዎ፡”

አለ።—አርታዒ።] እንግዲያውስ ወደ ቤት ሂድና ኑር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ደህና ሁን። እግዚአብሔር ይባርክህ።

126 እግዚአብሔርን ታምኛለሽ? [ያቺ እህት “አዎን፡ ጌታዬ፡ በእርግጥ አምናለሁ፡” አለች።—አርታዒ።] እግርሽ ላይ በህመም ትሰቃያለሽ። አንቺም፡ ከዚህ ከተማ ውጪ ነሽ። ከኦወንስቦሮ፡ ኬንታኪ ነሽ። ስምሽ ወይዘሮ ላምብ ትባያለሽ። ወደ ቤትሽ ተመለሺ ደህናም ሁኚ።

127 እንዲሁም እዚያ ጋር የተቀመጥሽው እመቤት፡ ከኦወንስቦሮ ነሽ። እዚህ በጡትሽ ላይ እብጠት አለብሽ። ነገ፡ ቀዶ ጥገና ይደረግበታል ተብሎ ይጠበቃል። እምነሽ፡ ሂጂ፡ ኑሪም።

128 ታምናለህ፡ ወዳጄ? [ያ ወንድም “አዎን፡ አምናለሁ፡” አለ።—አርታዒ።] አንዳችን ለሌላው እንግዳ ነን። ስምህ ሚስተር ጊልሞር ይባላል። ትክክል ነው። ታላቁ የቸርች ኦፍ ጋድ እንቅስቃሴ ካለበት፡ ከአንደርሰን፡ ኢንዲያና መጥተሃል። ትክክል ነው። እዚህ የተገኘኸው ግማሽ አካሏ ለታመመች ልጅህ ስትል ነው። በከፊል ሽባ ሆናለች። ታምናለህ? እንግዲያውስ ወደ ቤትህ ሂድ እንደ እምነትህም ሆና አግኛት። በጣም ጥሩ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እምነት ይኑርህ። እመን።

129 በሙሉ ልብህ ታምናለህ፡ ወዳጄ? [ያ ወንድም “አዎን፡ ጌታዬ፡” አለ።—አርታዒ።] አንተ ከኢንዲያናፖሊስ ነህ። አንተ የወንጌል አገልጋይ ነህ። እሷም ሚስትህ ነች። ኧሃ-ሃህ። እሷም እየተሰቃየች ነው። በጉሮሮ ውስጥ የኢሶፈገስ ችግር አለባት። ሐኪሙም… የልብ ችግር፡ ጭንቀትም። በጆሮዋ ውስጥ መስማት የተሳናት ሆና እያታለሁ። እ… ወዲህ ነይ።

አንተ ደንቆሮ መንፈስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ በሕያው አምላክ አዝሃለሁ፡ ከሴቲቱ ውጣ።

አሁን በደንብ ትሰሚኛለሽ። ሁለታችሁም ወደ ቤታችሁ ሂዱ ተፈወሱም። ወደ ቤታችሁ ተመለሱ። ትሰሚኛለሽ፡ ተፈውሰሻል። ደህናም ትሆኛለሽ።

130 በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? በእግዚአብሔር ብቻ እምነት ይኑርሽ። እመኚ።

131 ይህ የቆዬ አርቲራይተስ እና ሌላ ሁሉ እጅግ ከባድ ነው። እግዚአብሔር እንደሚያድንሽ ታምኛለሽ? እንግዲያውስ እዚያ ጋር ተራመጂ። ስሙን እያከበርሽ፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡” እያልሽ፡ ወደ ቤትሽ ተመለሺ።

በፍጥነት የቀለብኩት ምክንያት፡ ይህች ሴት ተመሳሳይ ነገር፡ አርትራይተስ ነበረባት።

እግዚአብሔር እንደሚያድንሽ ታምኛለሽ? [ያ ወንድም “አዎን፡” አለ።—አርታዒ።] እሺ፡ ወዳጄ። እንግዲያውስ እዚያ ጋር ተራመጂና፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡” እያልሽ፡ ወደ ቤትሽ ሂጂ።

132 እሺ፡ እህቴ፡ ዝም ብለሽ ተመልሰሽ፡ እመኚ። እዚህ ጋር፡ ጉልበትሽ ላይ ድርቅ ብሏል፡ የልብ ችግርም፡ ሌላም አለብሽ። ዝም ብለሽ ወደ ቤትሽ ተመለሺና፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡” በይው፡ ተፈወሺም። በሙሉ አቅምሽ እመኚ።

133 ታምናላችሁ? እናንተስ፡ እዚያ ጋር ያላችሁ፡ ሰዎች ሆይ ታምናላችሁን?

134 አንቺ እዚያ ጋር የተቀመጥሽው፡ ባለ-ጥቁር ጸጉር እመቤት፡ የሚጥል በሽታ አለብሽ፡ እግዚአብሔር እንደሚያድንሽ ታምኛለሽ? ተቀብለሻል? በጣም ጥሩ። ከተቀበልሽ፡ ይፈውሰሻል።

135 ይህ ሰባኪ፡ እዚ ተቀምጧል፡ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይፈልጋል። ወዳጄ፡ እንዲሁ አይደለምን? እግዚአብሔር እንደሚያደርግልህ ታምናለህ? እጅህን አንስተህ "ተቀብያለሁ፡" በል። ኧሃ-ሃህ።

136 እዚህ የተቀመጠች እመቤት፡ እጇን ወደ ታች አድርጋለች። የምታስበው መንፈሳዊ ችግር አለባት። ትክክል ነው።

137 ይህች ሴት ደግሞ፡ ልጄን እወልዳለሁ ወይ ብላ እየተጨነቀች ናት። ልክ ነው። ከሰብሰባዎቹ በአንዱ ላይ ነበርሽ። ልጅ ትወልጃለሽ ብዬ፡ በእግዚአብሔር፡ ቃል ገባሁልሽ። አላልኩሽም? በጣም ጥሩ። እንግዲያውስ ወደ ቤትሽ ሂጂ ውለጂም። ከእንግዲህ ሰለሱ አትጨነቂ።

138 በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ፡ ሁላችሁም? እያንዳንዳችሁ ታምናላችሁ? የአብርሃም ዘር የጠላትን ደጅ፡ ደጁን ይወርሳል። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ የአብርሃም ዘር ናችሁን? ከሆናችሁ እጃች ይነሱ።

እንግዲያውስ በአጠገባችሁ ባለው ሰው ላይ፡ እጆቻችሁን አኑሩ፡ እርስ በእርሳችሁ ላይ። እጃችሁን እርስ በእርሳችሁ ጫኑ። አሁን ደጁን ውረሱት። የእናንተ ነው። የራሳችሁ ነው። "የእምነት ጸሎት የታመሙትን ያድናል። እግዚአብሔር ያስነሣቸዋል።" እሺ፡ በየመንገዳችሁ ጸልዩ። በቤተክርስቲያንህ ውስጥ በምታውቁት መንገድ ጸልዩ። ክከእናንተ ጋር ሰላሉ ሰዎች ጸልዩላቸው። እርስ በርሳችሁ እጆቻችሁን ጫኑ እና ጸልዩ።

139 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በታላቁ፡ ሁሉን ቻይ በሆነው የንጉሣዊው ዘር ስም መጥተናል፡ በግ ባዘጋጀህበት ተራራ ላይ ተሰፋ የተገባለት፡ የአብርሃም ዘር፥ ትናንትና፡ እነዚያን ሽኮኮዎች እንዳስቀመጥካቸው፡ ያንን በግ በምድረ በዳ አስቀመጥክለት፡ ሚስጥራዊ ነው።

አቤቱ አምላክ ሆይ፡ ኃይልን፡ እምነትን፡ እንድትልክ እጸልያለሁ። እና እያንዳንዱ ዘር... ጌታ ሆይ፡ አንተ ተናግረሃልና፡ "የአብርሃም ዘር፡" እንዲሆኑ አውቃለሁ። እናም ዘር ሳይሆኑ፡ ዘር ስለመሆናቸው እያስመሰሉ የነበሩ እዚህ ካሉ፡ ሰለ አሳባቸው፡ ወይም ሰለማስመሰላቸው ይቅር በላቸው። እናም መንፈስ ቅዱስ አሁን ነፍሳቸውን በህያው እምነት ያቀጣጥል። መንፈስ ቅዱስ ወደ ሁሉም ልብ ይግባ እና እዚህ ያሉትን ሁሉንም ይፈውስ። እርስ በርሳቸውም እጃቸውን ጭነዋልና።

የንጉሥ ዘር ተናግሯልና፡ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። በታመሙ ሰዎች ላይ እጃቸውን ከጫኑ፡ ይድናሉ።" ያንን ቃል የገባውም፡ ህያው መሆኑን እያሳየ አሁን በዚህ አለ። እርስ በእርሳቸው እጃቸውን የጫኑ ዘር እነዚህ ናቸው። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" መንፈስ ቅዱስ በእጃቸው፡ በሰዎች ልብ ውስጥ፡ በአካላቸው ውስጥ ይሰረጽ፡ በመለኮታዊ መገኘት ውስጥ ያሉትን ሁሉ ይፈውሳቸው። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

ዲያብሎስን እገሥጻለሁ። አለማመንን ሁሉ እገሥጻለሁ። ርኩስ መንፈስን ሁሉ እገሥጻለሁ። አስመሳይን ሁሉ እገሥጻለሁ። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር

የሚቃረንን ሁሉ እገሥጻለሁ። መንፈስ ቅዱስም በእምነት፡ አሁን፡ በሰዎች ልብ ውስጥ ቦታውን ይያዝ። ህመምና ደዌ ሁሉ፡ መከራ ሁሉ፡ ሕዝቡን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይልቀቅ። ኣሜን።

140 እንግዲህ፡ የአብርሃም ዘር፡ እናንተ በእግዚአብሔር ቸርነትና ረድኤት፡ የንጉሥ የዘር ሐረግ የሆናችሁ፡ እናንተ የተሰፋ ቃል የሆናችሁ፡ ሰንቶቻችሁ እጃችሁን በማንሣት፡ "የጠየቅኩትን ተቀብያለሁ፡" ትላላችሁ? አመሰግናለሁ። ያ ነው። የተሰፋው ቃል ለዚህ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ባዳናችሁ፡ የሁሉ ወራሽ ትሆኑ ዘንድ፡ የተሰፋው ቃል የተሰጠው ለዚያ ነው። ከኃጢአት አዳናችሁ። ከበሽታ አዳናችሁ። ከሞት አዳናችሁ። ከሲኦል አዳናችሁ። ከመቃብር አዳናችሁ።

141 እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኛ ሁላችንም ወደ መቃብር እንገባለን።" ነገር ግን መቃብር አይዘንም። ወደ እርሱም ደግሞ፡ ሄዷልና፡ ይይዘው ዘንድ ግን አልቻለም። በትክክል። ሊይዘው አይችልም።

142 "እሺ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እጅግ ተፈትኛለሁ።" እርሱም፡ እንዲሁ። እናንተን ግን ከፈተና አዳናችሁ።

143 "ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን።" አያችሁ፡ ሰርቶላችኋል። ሁሉ የእናንተ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ ሁሉም ነገር የእናንተ ነው። እሱ ሁሉንም ነገር፡ በነጻ ሰጥቶአችኋል። ምንም ክፍያ፡ ወይም ሌላ ነገር የለውም። አሁን እንዲሁ የእናንተ ነው። በዚህ ደስ አይላችሁምን? በሱስ ደስ አይላችሁምን? እግዚአብሔር ይመስገን።

144 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ አገልግሎቶች፡ ይኖራሉ። አዎን። ዛሬ ማታ ነው፡ ዛሬ ማታ ሰባት-ተኩል ነው። ፓስተሩ እንዲያስተዋውቃችሁ ልፍቀድለት። ና ወደዚህ። ና ወደዚህ።

አሁን፡ በሚቀጥለው እሁድ ጥዋት፡ ደጉ ጌታ ቢፈቅድ፡ በተበርናክሉ ላሉ፡ ወይም ለሌሎች፡ ለታመሙ ለመጸለይ እመለሳለሁ።

59-1108 የጠላት ደጆችን መውረስ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2025 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org